# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 237 ሚያዝያ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ‹‹ኢትዮጵያን ለማስቀጠል ትውልዱ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል››

- ልጅ ዳንኤል ጆቴ
የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት


ፎቶ ፡- ናሆም አየለ

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- የጀግኖች አባቶች የመስዋዕትነት ውጤት የሆነችውን ኢትዮጵያን ለማስቀጠል ትውልዱ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመፃሕፍት አገልግሎት ዛሬ እየተከበረ የሚገኘውን 81ኛው የኢትዮጵያ የድል በዓል ቀንን ምክንያት በማድረግ የጀግኖች አርበኞችን ተጋድሎ የሚዘክር አውደ ርእይ ትናንት በከፈተበት ወቅት ልጅ ዳንኤል ጆቴ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያን ለማስቀጠል ትውልዱ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

ጀግኖች አርበኞች ደማቸውን አፍስሰው ያቆዩአትን ኢትዮጵያን ለማስቀጠል የአሁኑ ትውልድ ፍቅርንና መቻቻልን ከጀግኖች አባቶቹ ተምሮ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን በአንድነት ሊሻገር ይገባል ብለዋል ልጅ ዳንኤል ጆቴ፡፡

«ኢትዮጵያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በግብርናው ዘርፍ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ አበረታች መሆኑን ቋሚ ኮሚቴው ገለጸ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ከቡና፣ ከሻይ፣ ከቅመማ ቅመምና ከአበባ ምርት እንዲሁም ከሌሎች የግብርና ምርቶች ኤክስፖርት አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ መገኘቱ አበረታች መሆኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ገለጸ፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማትን የዘጠኝ ወር ሪፖርት በትላንትናው ዕለት በገመገመበት ወቅት በሰጠው ማጠቃለያ እንደገለጸው፤ በግብርናው ዘርፍ ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶች አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ መገኘቱ የሚያበረታታ ነው፡፡

በግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት ሆነው የተደራጁት የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ የሕብረት ሥራ ማህበራት ኮሚሽን እንደ ቅደም ተከተላቸው በዶክተር አዱኛ ደበላ እና በኮሚሽነር ፍሬዓለም ሽባባው የዘጠኝ ወር የሥራ አፈፃፀማቸውን

በግብርናው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ትውልዱ ከቀደሙ አባቶች የአገር አንድነት ማጽናትን መማር እንደሚገባው ተጠቆመ

አዲሱ ገረመው




አዲስ አበባ፡- ትውልዱ ልዩነትን ትቶ አገርን ካጸኑ አባቶች የአንድነት መንፈስ ሊማር ይገባል ሲሉ አባት አርበኛ ዳኛቸው ተመስገን ተናገሩ።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር አባል አባት አርበኛ ዳኛቸው ተመስገን የአርበኞች የድል በዓልን ምክንያት በማድረግ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ትውልዱ በልዩነት እንዲራመድ ተሰብኳል። ይሁንና ይህን ክፉ ሃሳብ ትቶ አገርን በደምና በአጥንታቸው ካጸኑ አባቶች የአንድነት መንፈስ ሊማር ይገባል።

ጀግኖች አርበኞች ልዩነት ሳይገድባቸው፤ ፈተና ወደ ኋላ ሳይጎትታቸው፣ ብሄር፣ ሃይማኖትና ጎሳ ሳይለያቸው ጠላት አገርን ለመውረር በመጣ ጊዜ ሁሉ መከትው መልሰዋል፡፡ ድሉ የተገኘው ልዩነትን ወደ ጎን በመተውና አንድነትን በማጠናከር በመሆኑ ትውልዱም ከዚህ ተምሮ አገርን የማስቀጠል ታሪካዊ ኃላፊነት አለበት ብለዋል፡፡

እንደ አባት አርበኛው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ለምና የበፖለቲካውም ስትራቴጂክ ቦታ ላይ እንደመሆኗ ጠላቶቿ በየጊዜው የተለያዩ ሴራዎችን ለማሴርና የጀርባ

የአገር አንድነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የብረት አምራቾችን የጥሬ ዕቃ ችግር ለማቃለል ግብአቶቹን ከመከላከያ ሚኒስቴር ሊያገኙ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የብረት አምራቾችን የጥሬ ዕቃ ችግር ለማቃለል ከመከላከያ ሚኒስቴርና ከስሩ ካሉ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ግብዓት እንዲያገኙ ከስምምነት ላይ መደረሱን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ።

የማዕድን ሚኒስቴር ከብረት አምራቾች ጋር ባደረገው ውይይት የጥሬ ዕቃ ችግራቸውን ለመቀነስ ግብዓቱን ከመከላከያ ሚኒስቴርና በስሩ ካሉ ተቋምት ጋር በማስተሳሰር እንዲጠቀሙ ለማድረግ ስምምነት ላይ መደረሱን ኢንጂነር ታከለ ኡማ ትናንትና አስታውቀዋል።

ለዓመታት ተከማችተው የቆዩ የወዳደቁ ብረቶችን ወደ ምርት መቀየር በአፋጣኝ ችግሩን ለማቃለል እንደሚረዳና ብረቶቹ ወደ አምራቾቹ በፍጥነት መቅረብ እንደሚጀምርም ተጠቁሟል።

በዘላቂነት ደግሞ በሀገር ውስጥ የብረት ማዕድንን ለማውጣትና አምራቾች ጥሬ ግብአቱን ከሀገር ውስጥ ማግኘት እንዲችሉ እንቅስቃሴ መጀመሩንም ሚኒስትሩ በማህበራዊ ገፃቸው አሳውቀዋል።

በተያያዘ ኢትዮጵያ በደቡብ አፍሪካ በሚካሄደው



ዓለም አቀፍ የማዕድን ጉባኤ ላይ የማዕድን ሀብቷን በሰፊው ለማስተዋወቅ ዝግጅቷን ማጠናቀቋን ኢንጂነር ታከለ ዑማ ገልጸዋል፡፡

ኢንጂነር ታከለ ዑማ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት እንዳስታወቁት፤ ከቀናት በኋላ በዓለም አቀፍ ደረጃ በደቡብ አፍሪካ በሚካሄደው "In-vesting in African Mining (INDABA)" የማዕድን ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ የማዕድን ሀብቷን በሰፊው ለማስተዋወቅ ዝግጅቷን አጠናቃለች።

ጉባዔው በአፍሪካ ማዕድን ካፒታላይዜሽንና ተያያዥ የማዕድን ልማት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቁ የማዕድን ኢንቨስትመንት ኮንፈረንስ እንደሆነ መረጃዎች አመልክተዋል።

ጉባዔው ለኢንዱስትሪው የወደፊት ርምጃ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው የማዕድን ሚኒስቴር ገልጾ፤ በማዕድን ዘርፉ አዳዲስ የልማት ስልቶችን፣ የንግድ ግንኙነቶችና የሌሎች አገራት ልምዶች የሚቀርቡበት መሆኑን ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

በተያያዘ ኢንጂነር ታከለ ከአውስትራሊያ አምባሳደር ጁሊያ ኔብሌት ጋር በጉባኤው ላይ በተናጠል የአውስትራሊያ የማዕድን ኩባንያዎች የውይይት መድረክ ለማዘጋጀት መስማማታቸውን ገልጸዋል።

በጉባኤው ላይ ኢትዮጵያ በሰፊው በማዕድን የወጪ ንግድን፣ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ማዕድናት እንዲሁም የኃይል ማዕድናትን በማስተዋወቅ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ እቅድን ለማሳካት ግዙፍ የማዕድን ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ለመሳብ እንደምትሰራም ነው የገለጹት።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀው "Investing in African Mining (INDABA)" የማዕድን ጉባኤ ከግንቦት አንድ ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ለአራት ቀናት በደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን ከተማ ይካሄዳል።



# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ ቅነሳን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የገንዘብ ሚኒስቴር አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመንግሥትን በጀት ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውልና ፍሪያማ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት እንዲሰፍን የወጪ ቅነሳ ተግባራዊ እንዲያደርጉ የገንዘብ ሚኒስቴር አሳሰበ፡፡

የፌዴራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት ሲገመገም የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴ እንዳሳሰቡት የወጪ ቅነሳ ጉዳይ የ2015 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ አዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች እንደማይኖሩና ዩኒቨርሲቲዎች ያላቸው ንብረት ታውቆ በአንድ የመረጃ ቋት ውስጥ እንዲካተት ተደርጎ የገንዘብ ሚኒስቴር ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን በቀጣይ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት እንደሚዘረጉ አስረድተዋል፡፡

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ኢዮብ ተካልኝ በበኩላቸው ገንዘብ ሚኒስቴር የመንግሥት በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ የፕሮግራም በጀት ክትትልና ግምገማ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በተለይም የካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለማስተካከል የተለያዩ ሥራዎች ተግባራዊ እየተደረጉ መሆናቸውንና የፋይናንስ ስርዓቱን በሕጉ መሰረት ተግባራዊ ባላደረጉ የተቋማት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ላይ ርምጃ መውሰድ መጀመሩን ጨምረው አመልክተዋል፡፡

በበጀት ስሚ ፕሮግራሙ ላይ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ በገንዘብ ሚኒስቴር ከተቀመጠላቸው የበጀት ጣሪያ በላይ ያቀረቡ ሲሆን በምክንያትነት ካቀረቡት ጉዳዮች ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ፣ የምግብ፣ የሌሎች ሸቀጦችና የመድኃኒት ዋጋ መጨመር እንዲሁም ያልተጠናቀቁ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ሥራ መኖራቸው ከተጠቀሱት መካከል ናቸው፡፡

የተማሪዎች የምግብ አቅርቦትና ሌሎች የምግብ ሸቀጦች በአግባቡ መተመን ይቻል ዘንድ ዝርዝር ጥናት በባለሙያዎች ተጠንቶ ለውሳኔ ለበላይ አካል እንዲቀርብ አቅጣጫ የተቀመጠ ሲሆን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውጤታማ የሥራ አፈጻጸም እውን እንዲሆን የክትትልና የቁጥጥር ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተመላክቷል፡፡

# የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ለማሳደግ ትኩረት መስጠቱን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- የኑሮ ውድነት ችግርን ለመፍታት፣ የዜጎችን ገቢ ለማሻሻልና ጠንካራና ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ለመገንባት ምርታማነትን ማሻሻል አስፈላጊ እንደመሆኑ የሀገሪቱን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ለማሳደግ ትኩረት መስጠቱን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡



**አቶ መላኩ አለበል**

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል "ኢትዮጵያ ታምርት" መርሐግብርን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ ንቅናቄው በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች በመተግበር የሀገሪቱን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ከፍ እንዲል የማድረግ እድል አለው፡፡

የማህበረሰብ እድገት ምርታማነትን ከማረጋገጥ ውጪ የሚመጣ ባለመሆኑ እንደ ሀገር የገጠመውን የኑሮ ውድነት ችግርን ለመፍታት፣ የዜጎችን ገቢ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሻሻል እንዲሁም ጠንካራና ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ያለው ሀገር ለመገንባት ምርታማነትን ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

ንቅናቄው ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ሳይሆን ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመታት ድረስ የሚወስድና በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች ተግባራዊ ሆኖ የሀገሪቱን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ከፍ እንዲል የማድረግ እድል ያለው በመሆኑ ትኩረት ይሰጠዋል ብለዋል፡፡

ንቅናቄው የአምራች ኢንዱስትሪውን ማነቆዎች በመፍታት ለዘርፉ ዘላቂ ልማትና ተወዳዳሪነት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንደሚያግዝና ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩ ዘርፉ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ያለመ መሆኑንም አስታውቀዋል።

የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ በተቀናጀ፣ በተባበረና ሁሉን አቀፍ በሆነ መንገድ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ እንዲሁም አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ እንደሚያግዝም ተናግረዋል፡፡

"ኢትዮጵያ ታምርት" ሀገራዊ የንቅናቄ የአምራች ኢንዱስትሪውን ማነቆዎች ለመፍታት የሚያግዝና በአገራዊ እድገት ላይ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማድረግ የሚያስችል መርሐ-ግብር መሆኑንም ጠቁመዋል፡

ከዚህ ቀደም 446 የሚደርሱ ኢንዱስትሪዎች በተለያየ ምክንያት ሥራ አቁመው እንደነበር ያስታወሱት አቶ መላኩ፤ በክልሎች በተደረገው ንቅናቄና ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት በተሰራው ሥራ 118 የሚደርሱ ኢንዱስትሪዎች ወደ ማምረት ሥራቸው እንዲገቡ ተደርጓል፣ የቀሩ ኢንዱስትሪዎችም በቀጣይ በሚተገበሩ የንቅናቄ ሥራዎች ወደ ምርት እንዲገቡ ይደረጋል ብለዋል፡፡

በመግለጫቸው የሀገሪቱ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ዝቅ ያለ መሆኑን ያመለከቱት አቶ መላኩ፤ ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅማቸው በአማካኝ ግማሽ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የግብዓት፣ የፋይናንስ፣ የመሰረተ ልማት አለመሟላት፣ የሰው ኃይልና የመንግሥት የተቀናጀ አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ምክንያት ምርታማ ያልሆኑ ኢንዱስትሪዎች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ብቻውን መፍታት ባለመቻሉና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ባለቤት እንዲኖራቸው ለማስቻል የንቅናቄ ስርዓት በመዘርጋት መፍታት ተገቢ መሆኑን ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡

በመሆኑም በሁሉም ዘርፍ ምርታማነትን በማረጋገጥ ለሀገሪቱ የብልጽግና ጉዞ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግም ጠይቀዋል።

ቀደም ብሎ "ኢትዮጵያ ታምርት" ንቅናቄ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ኦሮሚያ፣ በአማራ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎችና ድሬዳዋ ከተማ ውስጥ ሲካሄድ በመቆየቱ በበርካታ ጉዳዮች ላይ መግባባት በመፍጠር በዘርፉ ያሉ ማነቆዎች እንዲፈቱ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፣ ንቅናቄው ችግሮችን ሊፈታ እንደሚችልና ድጋፉ ሁለንተናዊ መሆኑን አቶ መላኩ ተናግረዋል።

ንቅናቄው ቀድሞ በክልሎች የተጀመረ ቢሆንም ሚያዝያ 29 ቀን 2014ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ይካሄዳል። በኢትዮጵያ ታምርት ሀገራዊ ንቅናቄ ማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ በዘርፉ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት እንዲሁም 81 ለሚደርሱ ድርጅቶች እውቅና እንደሚሰጥ ተገልጿል።



ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው

# ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሂደቷን ተሻግራ ስለኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወጣቱ የሚያስብባት አገር ማድረግ ያስፈልጋል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፦ኢትዮጵያ አሁን የምትገኝበት ጊዜ የፖለቲካ ሂደቷን ተሻግራ ስለ ልማት እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወጣቱ የሚያስብባት አገር ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ተናገሩ።

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው የሚያዝያ 27 የድል በዓልን አስመልክቶ በተደረገው ውይይት ላይ ባቀረቡት ጹሁፍ እንደጠቆሙት፤ በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ወጣቱ ማተኮር ያለበት ስለፖለቲካ ሥራ ወይንም ሌላ ትውልድ ስላወረሰው የፖለቲካ የቤት ሥራ ሳይሆን ስለልማት እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሆን አለበት።

ለወጣቱ ትውልድ ከዓለም አቀፍ ሥርዓቱ ጋር እኩል በሚሄድበት እና ሀገርን ከፍ በሚያደርግበት ሁኔታ ላይ የፖለቲካ የቤት ሥራ የመስጠት አደራ አለብንም ብለዋል።

ዛሬ 81ኛው የድል በዓል የሚከበረውም እንግሊዞች ከኢትዮጵያ ጎን በመሰለፍ በሶስት ግምባር በኬንያ የካኒንግሃም ጦር፣ በካርቱም የጌድዮን ጦር እንዲሁም በከሰላ አስመራ ግምባር ጣሊያንን ሲያጠቁ፤ የካኒንግሃም ጦር መጋቢት 28 1933 ቀድሞ አዲስ አበባ ሲገባ የእንግሊዝን ባንዲራ በመስቀሉ ሙሉ ነጻነት እንዳልነበረ አስታውሰዋል፡፡

ሚያዝያ 27 ቀን 1933 የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፍቼ ተነስተው እንጦጦ ሲደርሱ የእንግሊዝ ባንዲራ በኢትዮጵያ ባንዲራ ተተክቶ ሙሉ ነጻነት የታወጀበት በመሆኑ ነው። ከሚያዝያ 27 1933 እስከ 1934 ድረስም ንጉሰ ነገስቱ ካቢኔ ቢሰይሙም ገንዘብና መጓጓዣ አልነበራቸውም፡ ፡ የእንግሊዝ የጦር አለቆች ሁሉንም ነገር እስከ 1942 ሚያዙበት ስለነበር ትልቅ የዲፕሎማሲ ትግል ተደርጓል ብለዋል።

በ1942 ስዊዝ ካናል ላይ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ፍራንክሊን ዲላኖ ሩዝቬልት የአሜሪካን ፕሬዚዳንትን ጋር በአንድ የአሜሪካን የጦር መርከብ ላይ ባደረጉት ውይይት ኢትዮጵያ እራሷን የቻለች ነጻ አገር መሆኗን ያዘዙና ተጽዕኖ የፈጠሩ መሆኑን ታሪክ የማይረሳው እንደሆነም ተናግረዋል።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን በበኩላቸው ሚያዝያ 27 የሚከበረው የድል በዓል ኢትዮጵያውያን በደምና በአጥንታቸው አንድነቷን አስጠብቀው ያቆዩአት ሀገር መሆኑን ለትውልዱ አስመስክረዋል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያን ለማፍረስ አንዴ በሃይማኖት ሌላ ጊዜ በብሔር እየተሞከረ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንካራ ባህልና ሃይማኖት ያለው በመሆኑ የሚከፋፍለውን ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን የሚያስተናግድ ሕዝብ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የዘንድሮው 81ኛው የሚያዝያ 27 የድል በዓል ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በከፍተኛ ደረጃ እንደምታከብረው ሁሉ የመከላከያ ጦር አብሮ ተሰልፎ የኢትዮጵያን ትልቅነት በሚያሳይ ደረጃ በደማቅ ሥነሥርዓት የሚከበር ይሆናል።

ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ሳውቃት ጠንካራ አንድነቷ በመሆኑ ይህን ባህላችንን ለፖለቲካ ዓላማ እንዳንጠቀም ሁላችንም ዘብ መቆም ይገባል ሲሉም አመልክተዋል።

# ፓርቲው በአገራዊ ምክክሩ አጀንዳዎች ላይ የሚሳተፉ ኮሚቴዎችን እያቋቋመ መሆኑን ገለጸ

*ሙሳ ሙሐመድ*

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ በሚካሄደው ብሔራዊ ምክክር እያንዳንዱ አጀንዳዎች ላይ የሚሳተፉ ኮሚቴዎችን በድርጅቱ ውስጥ እያቋቋመ መሆኑን የነፃነትና እኩልነት ፓርቲ አስታወቀ፡፡

የድርጅቱ ሊቀመንበር ዶክተር አብዱልቃድር አደም እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በቀጣይ በሚካሄደው ብሔራዊ ምክክር እያንዳንዱ አጀንዳዎች ላይ የሚሳተፉ ኮሚቴዎችን እያቋቋመ ነው፡፡


ፓርቲው በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ በብሔራዊ ምክክሩ ውስጥ በያንዳንዱ አጀንዳዎች ላይ የሚሳተፉ ኮሚቴዎችን ከፓርቲው ፕሮግራሞች በመነሳት እያቋቋመ ነው፡፡

በእያንዳንዱ የምክክሩ አጀንዳዎች ላይ ከድርጅቱ መርሐ ግብር በመነሳት ድርጅቱ የሚይዛቸውንና ትክክል ናቸው ተብለው የሚታመንባቸውን አቋሞች ላይ ሰነድ እያዘጋጀ መሆኑን ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዶክተር አብዱልቃድር ማብራሪያ ፓርቲው በሚይዛቸው አቋሞች ላይ እንደ የህገ-መንግሥት ማሻሻል፣ ግጭቶች እንዴት ይፈታሉ፣ ልማት እንዴት ይመጣል፣ አብሮነት እንዴት ይጠናከራል፣ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዴት ይጎለብታል፣ ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዴት ይሰፍናል በሚሉና በመሳሰሉት አጀንዳዎች ላይ ከወዲሁ በዝርዝር በባለሙያ በታገዘ መልኩ ሰነዶች እየተዘጋጁ ነው፡፡

ድርጅቱም በምክክሩና በውይይቱ ሂደት የሚፈጠረውን አማካኝ ውጤት ተከትሎ በቀጣይ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

በአገራዊ ምክክሩ የፓርቲያችን ብቻ ሳይሆን የሌሎችም ፓርቲዎችና ግለሰቦች ፍላጎት እንዲከበር ለማድረግ መስራት ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር አብዱልቃድር፤ ይህ እንዲሳካ ፓርቲው እየሠራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡በምክክሩ እኔ ያላመንኩበት፣ እኔ ያሰብኩትና



ዶክተር አብዱልቃድር አደም

ያለምኩት ብቻ ይሁንልኝ ካልሆነ የሚል ግትር አቋም መያዝ ሳይሆን የሌሎችም ሀሳብና ጥያቄ እንዲከበርና አገራዊ ምክክሩ ፋይዳው የጎላ እንዲሆን ፓርቲያቸው እንደሚሠራም ጠቅሰዋል፡፡

ሰላም፣ መረጋጋት፣ ልማትና ብልጽግና ሊመጣ የሚችለው ሁላችንም አገራዊ ሰላምንና መረጋጋትን ለማምጣት ስንሰራ ብቻ ነውም ብለዋል፡፡

አገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆንና መግባባትን ለማምጣት ቅድሚያ መተማመን ያስፈልጋል፡፡ የምክክሩ የመጨረሻ ግቡም በፖለቲካ ኃይሎች መካከል ያለው የተለያየ ፍላጎትና ዓላማ መካከል መተማመንን ማምጣት ነው ብለዋል፡፡

በምክክሩ ሂደት ቅንነት የስፈልጋል፡፡ የኛን ሀሳብና አሰራር በትክክል አስረድተን፣ የሌሎችንም በትክክል አድምጠን፣ ተገንዝበንና ተረድተን ለአገር የሚበጀው የቱ ነው፣ አማካኝ ሃሳብስ የትኛው ነው፤ በማለት ጠቃሚ አገራዊ ሃሳብና አሰራር የሚበጅበት ነው፡፡ እኛ ምንድን ነው የምንፈልገው፣ ሌሎች ቡድኖች ምንድንነው የሚፈልጉት፣ ምንድንስ ነው ስጋታቸው የሚለውን ተረድተን የምንችለውን ያህል ለማሟላት ጥረት ማድረግ ይጠበቃል ያሉት ዶክተር አብዱልቃድር፤ ቡድኖችና ተሳታፊዎችም ሀሳባቸውን በተገቢው መንገድ በመረጃ አስደግፈው ማቅረብና ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ካደረጉ በኋላ መሀል መንገድ ላይ የሚያስማማንን ነጥብ በማበጀት የምንፈልገውን አገራዊ ሰላምና መረጋጋት፣ ለማምጣት ያስችለናል ብለዋል፡፡ ይህንን ማድረግ ካልቻልን አገራዊ ምክክሩ ሁላችንም ዳር ቆመን አንዱ የሌላኛው ላይ ሀሳቡን ለመጫን ከሆነ ትርጉም አይኖረውም ብለዋል፡፡

ፓርቲያችን ከውጥኑ ጀምሮ ብሔራዊ መግባባት ምን ማለት ነው፡፡ ችግሮች እንዴት ይቀረፋሉ፣ ምንምን አጀንዳዎች አሉ በሚል በጥናት ወረቀት አስደገፈን ሀሳቦችን እያቀረብን በተለያዩ መልኩ እየተሳተፍን ነው ያሉት ችግሮችም እየቀረቡ እየተስተካከሉ ምክክሩ ነጻ የሆነና ገለልተኛ እንዲሆን የቻልነውን ያህል እናደርጋለን ብለዋል፡፡

በሂደቱም የሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማህበራትና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በቅርበት መስራትን እንደሚጠይቅ ጠቁመዋል፡፡

የምክክሩ አጀንዳዎች ሲንከባለሉ የነበሩ ናቸው፣ በአሁኑ ጊዜ የደረሰንበት ሁኔታ ተስፋ ሰጪ ነው፡፡ ሂደቱ የሚፈልጋቸውን ፖለቲካዊና ህጋዊ ማዕቀፎች ጠብቆ እንዲሄድ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ የድርጅቱ ተሳትፎም የሚሆነው እውነተኛ ብሔራዊ መግባባት እንዲካሄድ ማደረግ ነው ሲሉም ሊቀመንበሩ ተናግረዋል፡፡

# የአውሮፓ ሕብረት ከቀረጥ ነጻ የንግድ ስርዓቱን ለፖለቲካ መሳሪያነት እንደማያውለው አስታወቀ

## - ኢትዮጵያ ከአጎዋ ብትታገድም ከአውሮፓ ነጻ የንግድ ስርዓት በሰፊው እንድትጠቀም ተጠየቀ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የአውሮፓ ሕብረት ለታዳጊ አገሮች ያዘጋጀውን ከቀረጥ ነጻ የንግድ ስርዓት /EBA/ ልክ እንደአሜሪካው አጎዋ ሁሉ ለፖለቲካ መሳሪያነት እንደማያውለው አስታወቀ።

ኢትዮጵያ ከአጎዋ ብትታገድም ከአውሮፓ ሕብረት ነጻ የንግድ ሥርዓት /EBA/ በሰፊው መጠቀም እንዳለባት ሕብረቱ ገልጿል።

የአውሮፓ ሕብረት ልዑክ የኢትዮጵያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ ትናንት ከጋዜጠኞች ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳስታወቁት፤ የአውሮፓ ሕብረት ለታዳጊ አገራት ያዘጋጀውን ነጻ የግንድ ስርዓት ለፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያነት የማዋል ፍላጎት የለውም።

Everything but arm (EBA) የተሰኘው የአውሮፓ ሕብረት ነጻ የንግድ ስርዓት ታዳጊ አገራት ማንኛውንም ዕቃ ወደአውሮፓ ሲያስገቡ ከቀረጥ ነጻ ዕድል እንዲጠቀሙ የሚያግዝ ነው። በተለይ ከታዳጊ አገራት የሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተጨማሪ ታሪፎች እንዳይጣሉ የሚያዝ አሰራር በመሆኑ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ አገራት እየተጠቀሙበት ይገኛል ብለዋል።

ይህንን የሕብረቱን ከቀረጥ ነጻ አሰራር ባልተፈለገ መንገድ በመጠቀም የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ፍላጎት የለም ያሉት አምባሳደሩ፤ ዋናው ነገር ዓለም አቀፍ የሰብዓዊና የሠራተኞች መብቶችን እያከበሩ መሥራት ነው ሲሉም አስረድተዋል።

ዓለም አቀፍ ሕግን አክብረው እስከሰሩ ድረስ ማንኛውንም ከጦር መሳሪያ ውጭ የሆኑ ዕቃዎች ወደአውሮፓ ያለምንም ታሪፍና ኮታ ማስገባት የሚቻልበት ዕድል መኖሩንም ገልጸዋል።

በመሆኑም ኢትዮጵያም የዕድሉ ሰፊ ተጠቃሚ እንድትሆን ላኪዎች ምርቶቻቸውን በስፋት ለአውሮፓ




ፎቶ ፡- ፎቶ ዳኜ አበራ

አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ

ገበያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል ሲሉ ጠቁመዋል።

በአውሮፓ ያለው የገበያ ዕድል ሰፊ በመሆኑ ኢትዮጵያ ከአጎዋ ብትታገድም ከአውሮፓ ሕብረት ነጻ የንግድ ስርዓት /EBA/ በሰፊው መጠቀም እንዳለባት የሕብረቱ ጽህፈት ቤት ዋና ተወካይ ገልጸዋል።

አንዳንድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ፋብሪካዎች ስለአውሮፓ ሕብረት ነጻ የንግድ ስርዓት ምንም አይነት መረጃ የላቸውም ያሉት አምባሳደር ሮላንድ፤ ይህንን መረጃ ለእያንዳንዱ አምራችና ላኪ ማድረስ ከመገናኛ ብዙሃኑ ይጠበቃል ብለዋል።

በተጨማሪ እስካሁን ባለው አሰራር ኢትዮጵያ የነጻ ንግድ ስርዓቱ ተጠቃሚ ብትሆንም፤ ካላት አቅምና አስቻይ ሁኔታዎች አንጻር ግን ገና በሰፊው መጠቀም አለባት። ለዚህም ደግሞ ጥራት ያላቸውን ምርቶች እያዘጋጁ መላክ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የአውሮፓ ህብረትም ነጻ የንግድ ስርዓቱን ይበልጥ ክፍት በማድረግ አገራት አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ይደግፋል። ለኢትዮጵያውያን አምራችና ላኪዎችም ጥራት ያላቸውን ምርቶች አዘጋጅተው እንዲልኩ የተለያዩ ስልጠናዎችንና ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በ2020እ.ኤ.አ. ወደ አውሮፓ ሕብረት አባል አገራት ከላከቻቸው ምርቶች 543 ሚሊዮን ዩሮ ስታገኝ ከዚህ ውስጥ 270 ሚሊዮን ዩሮ የሚያወጡት ምርቶች ለታዳጊ አገራት በተዘጋጀው የቀረጥ ነጻ የንግድ ስርዓት በኩል የገቡ መሆናቸውን የሕብረቱ መረጃ አመልክቷል።

# በአማራ ክልል ከ91 ሺህ ኩንታል በላይ የበቆሎ ዘር እየተሰራጨ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ለመኸር እርሻ 91 ሺህ 776 ኩንታል የበቆሎ እና 40 ሺህ 687 ኩንታል የስንዴ ዘር ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የክልሉ የግብርና ጥራትና ደህንነት ባለስልጣን ለ2014/2015 ዓ.ም የመኸር እርሻ በዋና ዋና የሰብል ዓይነቶች በቆሎ፣ስንዴ፣ጤፍ፣ የቢራ ገብስ እና ሌሎችም እንደተፈላጊነታቸው በላቦራቶሪ ፈትሾ የጥራት ደረጃ ያሟላ ዘር በግብርና ቢሮ በኩል ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ እያደረገ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡

የባለስልጣኑ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሞላ ካሳ እንደገለጹት፤ ለ2014/2015 ዓ.ም የመኸር እርሻ የሚሆን ምርጥ ዘር ከምርጥ ዘር አባዥ ድርጅቶች ዩኒየኖች፣ ሕብረት ሥራ ማህበራት፣ የግብርና ምርምር ማዕከላትና ዩኒቨርሲቲዎች የጥራት ቁጥጥር በማድረግ እያዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዚህ ዓመት ለመኸር እርሻ 91 ሺህ 776 ኩንታል የበቆሎ እና 40 ሺህ 687 ኩንታል የስንዴ ዘር በላቦራቶሪ ተፈትሾ የጥራት ደረጃ ያሟላ እና መለያ ምልክት ተሰጥቶ ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ መሆኑን ተናግረው፤ ተመሳስለው ገበያ ላይ ከሚሸጡ የጥራት ቁጥጥር ባልተደረገበት ዘር እንዳይታለሉ አሳስበዋል፡፡



በሌላ በኩል ለመኸር እርሻ የሚሆን ሰው ሰራሽ የአፈር ማዳበሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ እጥረት መከሰቱን ተከትሎ «ኢኮ ግሪን» የተሰኘ ፈሳሽ ማዳበሪያ በአማራጭነት በግብርና ሚኒስቴር እውቅና የተሰጠው በመሆኑ አርሶ አደሩ ከህብረት ሥራ ማህበራት እና ከእርሻ አገልግሎት ማዕከላት ብቻ በመግዛት መጠቀም እንደሚችሉ መናገራቸውን ከአማራ ኮሙዩኒኬሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

## ‹‹ኢትዮጵያን ለማስቀጠል...

ከገፅ 1 የዞረ

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ የቀድሞ አባቶች በጀግንነት፣ በመቻቻል፣ በመዋደድ እና በፍቅር ሀገርን ለማቆም ሲሉ የነፍስ ዋጋን ከፍለዋል፤ አሁን ያለው ትውልድም ኢትዮጵያ የጀግና አባቶች የመስዋዕትነት ውጤት የሆነችውን ኢትዮጵያ ለማጽናት ኃላፊነት አለባቸው።

ጀግኖች አርበኞች ዋጋ ከፍለው አገር እንዳስቀጠሉ ሁሉ የአሁኑ ትውልድም ከአርበኞች አንድነትን ትብብርን እና ጀግንነትን በመማር አገርን ለቀጣይ ትውልድ ማኖር ይገባቸዋል ብለዋል። የጀግኖች አርበኞች ታላቅ አደራ የሆነችው ኢትዮጵያ ጸንታ ለቀጣይ ትውልድ እንድትሸጋገር ሁሉም ሰው ዘብ ሊቆም ይገባል።

ኢትዮጵያን በሚመለከት ጉዳይ እያንዳንዱ ዜጋ መንግሥት ነው፤ ሀገርን ለመንግሥት ብቻ መተው አይገባም ሲሉም ተናግረዋል።

«ኢትዮጵያ እንድትቀጥል ከፈለግን የምንሰማውን ነገር በብዙ ወንፊት እያጣራን ልናደምጥ ይገባል» ያሉት ልጅ ዳንኤል፤ ለሀገር ሰላም መስፈን ሁሉም ህብረተሰብ የየግሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክትም ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመፃህፍት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ይኩኖ አምላክ መዝገቡ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ተቋሙ ጀግኖች አርበኞችን የሚዘክር ሥራ በመስራቱ ትልቅ ኩራት ይሰማዋል።

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመፃሕፍት አገልግሎት የከፈተው አውደ ርዕይ ጀግኖች አርበኞች አገርን ለማስቀጠል የከፈሉትን ዋጋና በአንድነት መሻገር የማይቻል ችግር እንደሌለ ለትውልዱ ለማስተማር ያለመ ሲሆን፤ እስከ ሚያዝያ 28 ድረስ እንደሚቀጥል ተገልጿል።

## ትውልዱ ከቀደሙ...

ከገፅ 1 የዞረ

ተንኮል ለመስራት አቅደው ይንቀሳቀሳሉ። በተለይም በቀይ ባህርን ተንተርሶ በሚመጣ ፖለቲካ የተነሳ ግንባር ቀደም የትኩረት ማዕከል መሆኗ አይቀርም።

ስለዚህም ከፋፋይ ሴራዎችን ሁሉ አሽንፎ ለመጓዝ ልክ እንደአባቶች አንድነትን አጥብቆ መያዝ ያስፈልጋል። ወራሪ በመጣ ጊዜ ሁሉ ይህ አንድነታችን ነው አሸናፊ ያደረገን ብለዋል።

ጠላት በአድዋ ድል ወቅት በሰማይና በመሬት በዘመናዊ መሳሪያና ትጥቅ ታግዞ ጥቃት ቢፈጽምም፤ አባቶች ከልዩነታቸው ታቅበው አገርን በማስቀደም በእግራቸው ጭምር በመጓዝ ታላቅ ተጋድሎን ፈጽመዋል። ከዚያ በኋላ የነበሩትም አባቶች ይህንኑ ደግመዋል፤ ትውልዱም ከዚህ ብዙ ሊማር ይገባል።

በወቅቱ አባቶች ጠላትን ድል ለማድረግ የነበራቸው ቁልፍ ጉዳይ አንድነታቸው ነበር ያሉት አባት አርበኛው፤ ጣሊያን በአድዋ ከተሸነፈ በኋላ በተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች የነበሩት መሳፍንትና መኳንንቱ እርስ በእርሳቸው ይጋጩ ነበር። ነገር ግን ጠላት ዳግም ሲመጣ ብሄር፣ ሃይማኖትና ጎሳ ሳይለዩ ስለ ልዩነታቸው ከድል በኋላ ለመወያየት ቀጠሮ ይዘው አገርን በማስቀደም ነበር ጠላትን መፋለም የቻሉት ሲሉ አስረድተዋል።

በወቅቱ ይጣላ የነበረው፣ በመሬትና በሚስት ይጋደል የነበረው፤ እኔ ነኝ የበላይ የሚለውና ይጋጭ የነበረው ሁሉ ጠላት በመጣ ጊዜ ግን የእርስ በእርስ ሽኩቻውን አቁሞ ጠላትን በመፋለም አገር ማጽናት ችሏል ሲሉ ገልጸዋል።

ከጦርነት በኋላ ገበሬው ባለው አቅም አርሶ እንዲበላ፣ አንዱ ከሌላው ጋር በመተዋወቅ ብሄር፣ ሃይማኖትና ጎሳ ሳይለዩ በአንድነትና በፍቅር አገራቸውን በመጠበቅ ለዛሬው ትውልድ ማቆየታቸውን ተናግረዋል።

ይህም አንድነት ኃይልና ፍቅርን ያሳየ በመሆኑ አዲሱ ትውልድም የአባቶቹን ዓርአያ በመከተል አገሩን የሚያጸናበትን የአንድነት ኃይል አጥብቆ ሊይዝ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

አባት አርበኛው፤ ትውልዱ "አባትህን ጠይቅ ይነግርሀል" የሚለውን ብሂል መጠቀም እንዳለበት በመምከር፤ አባቶች ምን ያህል ፈተና ውስጥ ሆነው ጠላትን ማሸነፍ እንደቻሉም ጭምር ትውልዱ በሚገባ መማር አለበት። ታሪካቸውን በአግባቡ ሲያውቁም ጻብና ክርክርን ትተው ለወገን የሚጠቅመውን ፍቅርና አንድነትን መላበስ ይችላሉ ብለዋል።

## በግብርናው ዘርፍ ...

ከገፅ 1 የዞረ

ለቋሚ ኮሚቴው አቅርበዋል።

ቋሚ ኮሚቴው ሪፖርቱን ከአዳመጠ በኋላ ቀደም ብሎ ካደረገው የመስክ ጉብኝት ጋር በማጣመር የየተቋማቱን ጠንካራና ደካማ ሥራዎች ለይቶ አሳይቷል። በሁለቱ ተቋማት በኩል የታዩ ጠንካራ ጎኖች የሚበረታቱ መሆኑንና ሊስተካከሉ ይገባቸዋል ያላቸውን በዝርዝር አስቀምጧል።

የግብርና ምርቶች በዚህ ደረጃ የውጭ ምንዛሪ ማምጣት መቻላቸው የተቋማቱ ድምር ውጤት መሆኑንና ከዓምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የታየው ለውጥ አበረታች ነው ብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሰሎሞን ላሌ በማጠቃለያው እንደገለፁት፤ በምግብ ራስን መቻል እና የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ምርቶችን ማምረት ለግብርናው ዘርፍ የተሰጠ ኃላፊነት ነው። እንዲሁም የኢኮኖሚ ሽግግር በሀገሪቱ ማምጣት እና የሥራ ዕድል ፈጠራውም በግብርና ዘርፉ ይፈጠራሉ ተብሎ ነው የሚጠበቀው።

በቋሚ ኮሚቴው ግምገማ መሰረት ግብርና ሚኒስቴርም ሆነ ተጠሪ ተቋሙ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የውጭ ምንዛሪ ለሀገሪቱ በማስገኘት ረገድ ትልቅ ሥራ ሠርተዋል። በዘጠኝ ወራት ውስጥ በቡና ምርት ብቻ ዓምና ከነበረው 72 ነጥብ 7 በመቶ የውጭ ምንዛሪውን ማሳደጉ እጅግ በጣም ውጤታማ ሥራ መሆኑ ተነስቷል። በዚህም የቡና ምርትን ወደ ውጭ በመላክ ብቻ 894 ነጥብ 3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማስገኘት በመቻሉ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ችግር በመቅረፍ ረገድ ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ እንዳሉት፤ በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም በጋራ ሲታይ ዓምና በተመሳሳይ ወቅት



ከነበረው 525 ነጥብ 13 ሚሊዮን ዶላር ወደ 907 ነጥብ 15 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት መቻሉ ትልቅ እምርታ ነው።

በአጠቃላይ እንደ ሀገር ሲገመገም ባለፉት ዘጠኝ ወራት የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ትልቁን ድርሻ ተወጥቷል።

በተጨማሪም ባለሥልጣኑ ጥቂት የነበረውን የኢትዮጵያ ቡና ኤክስፖርት መዳረሻ ወደ 33 ሀገራት ማሳደጉ በጥንካሬ ተነስቷል።

በሌላ በኩል የአንድ ሄክታር አማካይ የቡና ምርት ሰባት ነጥብ አምስት ቢሆንም ቋሚ ኮሚቴው ወርዶ ባረጋገጠ ጊዜ አንዳንድ አካባቢዎች ደቡብ ምእራብ ለአብነት በሄክታር እስከ 15 ኩንታል በሄክታር ማምረታቸውን ገልጸዋል። ተቋሙ እነዚህን መሰል ተሞክሮዎች አጥንቶ ሊያስፋፋቸው ይገባልም ብሏል ቋሚ ኮሚቴው።

ሕገ ወጥ የቡና ዝውውር በርካታ የውጭ ምንዛሪ የሚያሳጣ ስለሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደረገው ቁጥጥር መጠናከር እንዳለበትም ተነስቷል።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ሕብረት ሥራ ማህበራት ኮሚሽን ያለፉት ዘጠኝ ወራት ሪፖርት በኮሚሽነር ፍርዓለም ሽባባው አማካኝነት ቀርቧል። ቋሚ ኮሚቴው ሪፖርቱን ካዳመጠ በኋላ ጠንካራና ደካማ ያላቸውን የዘጠኝ ወራት አፈፃፀም አስቀምጧል።

ሕብረት ሥራ ማህበራት የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት እና የአርሶ አደሩ ምርቶች በተገቢው ጊዜ እንዲነሱ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሰሎሞን ገልጸዋል። ሸማችንና አምራችን በአጠረ ሰንሰለት በማገናኘትም ሕብረት ሥራ ማህበራት ትልቅ አስተዋፅዖ እያረከቱ መሆኑን ገልጸዋል።

ተደራሽነት እና የአባል ብዛት በመጨመር ረገድ በዘጠኝ ወራት አፈፃፀሙ ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውንና የማደራጀት እና የማጠናከር ሥራዎችም አበረታች መሆናቸው ተገልጿል።

የሕብረት ሥራ ማህበራት አባላት ቁጥርንም አራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ማድረሱ በበጎ መልኩ የተነሳ ሥራው ሲሆን የአባላቱን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተሠራ ያለው ሥራ አበረታች እንደሆነም ተነግሯል። ከማዳበሪያ ሥርጭት ጋር ተያይዞ ማህበራት የሠሩት ሥራ ቋሚ ኮሚቴው በአካልም ወርዶ ያየው በመሆኑ በጥሩ ጎኑ ኮሚቴው በግብረ መልስ አንስቷል።

ከደላላ ጋር ተያይዞና ምርትን ለታሰበለት ዓላማ ሳይውል የመጥለፍ አዝማሚያዎች በጉድለት የሚታዩ በመሆኑ ማስተካከል እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው አሳስቧል። አምራቹና ሸማቹ ምርቱን በስግብግብ ነጋዴዎች እና በደላሎች እየተነጠቀ በመሆኑ በጣም አሳሳቢ ስለሆነ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባውም ተጠቅሷል።

በተያያዘ የዋጋ ሥርዓት ተበጅቶ ተመጣጣኝ የዋጋ ትመና ሊኖር ይገባል። ምንም ዓይነት እሴት ያልጨመረ ደላላ በመካከል እየገባ የዋጋ ንረት መፍጠሩን ለማስቆም በትብብር አመርቂ ሥራ ሊሠራ እንደሚገባም ተመላክቷል።

በሕብረት ሥራ ማህበራቱ ችግር ፈቺ ኦዲት ሊሠራ እንደሚገባውና ለዚህም ተቋማቱን በተማረ የሰው ኃይል መምራት እንደሚያስፈልግ ቋሚ ኮሚቴው አሳስቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አባቶቻችን አንድ ላይ የሞቱት እኛ በሰላምና በአንድነት እንድንኖር ነው!

ኢትዮጵያ የነጻነትና አንድነቷ ምስጢር የልጆቿ መስዋዕትነት ነው፤ በልጆቿ ደም ደምቃ የተጻፈች፣ በልጆቿ አጥንት የታጠረች፣ በልጆቿ የአርበኝነት ተጋድሎ ጸንታ የኖረች ነች፡፡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በለውጥ ማግስት የበዓለ ሲመታቸው የመጀመሪያ የፓርላማ ንግግራቸው ላይ እንዳስደመጡት፤ ኢትዮጵያዊነት ያስተማረን እውነታ በጊዜያዊ ችግሮች ተሸንፎ መውደቅን ሳይሆን ፈተናዎችን ወደ ዕድልና መልካም አጋጣሚ ቀይሮ ድል መቀዳጀትን ነው። ትላንት፣ አባቶቻችን በመተማ፣ በማይጨውና በካራ ማራ አጥንታቸውን ከስክሰው የከበረ ደማቸውን አፍስሰው በክብርና በአንድነት ያቆዩልን አገር አለችን። በዚህም እኛ ውብ አገርና አኩሪ ታሪክ ያለን፤ መነሻችንን የምናውቅ ሆነን የተሰራን ዕድለኞች ነን።

ለዚህ ደግሞ ውድ ዋጋ ተከፍሎልናል፤ ኢትዮጵያ እንድትጸና፣ ኢትዮጵያዊነት እንዲያብብ፣ የዛሬው የእኛ ትውልድ በፍቅርና አንድነት ከፍ ብሎ እንዲኖር የትናንት አባቶቻችን የሕይወት ዋጋ ከፍለውልናል፡፡ ከላይ በጠቀስኩት የጠቅላይ ሚንስትሩ ንግግር “አማራው በካራ-ማራ ለአገሩ ሉዓላዊነት ተሰውቶ የካራ-ማራ አፈር ሆኖ ቀርቷል። ትግራዋይ በመተማ ከአገሬ በፊት አንገቴን ውሰዱ ብሎ የመተማ አፈር ሆኗል። ኦሮሞው በዓድዋ ተራሮች ላይ ስለአገሩ ደረቱን ሰጥቶ የአገሩን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ከዓድዋ አፈር ተቀላቅሏል። ሱማሌው፣ ሲዳማው፣ ቤንሻንጉል፣ ወላይታ፣ ጋምቤላው፣ ጉራጌው፣ አፋሩ፣ ስልጤው፣ ከምባታው፣ ሀዲያው እና ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ በባድመ ከአገሬ በፊት እኔን ብለው እንደወደቁ ከባድመ አፈር ጋር ተዋህደዋል።” በሚል እንደተገለጸውም፤ ስለዛሬው ማንነታችን ከፍታ አባቶቻችን ያለ ልዩነት በአንድ ላይ ሞተውልናል፡፡

በጥቅሉ የቀደሙት አባቶቻችን ኢትዮጵያዊ ሆነው ኖረውባት፣ በመስዋዕትነታቸው ኢትዮጵያ ሆነው ያነጿትን አገር ለእኛ ሰጥተውናል፡፡ የሰጡን ግን በአንድነት ከፍ እንድንልባት፤ በፍቅር እንድንደምቅባት፤ በነጻነት ኮርተን እንድንራመድባት፤ በልጽገን ከልመና እንድንላቀቅባት፤ በወንድማማችነት፣ በአብሮነትና መተባበር የሚገለጸው የሕብረ ብሔራዊነታችን የጠበቀ ቁርኝትና ትስስር ሳይላላ በሚፈጥረው ልዕልና ታጅባ ለቀጣዩ ትውልድ እንድትተላለፍ ነው፡፡ የአያት አባቶቻችን የታሪክ ቅብብሎሽም የሚያስረዳንና የሚገልጽልን ይሄንኑ እውነት ነው፡፡

ምክንያቱም የቀደመውን ሥልጣኔ የመሰረቱት አባቶች ለቀጣዩ ትውልድ እያሳለፉ የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጀጎል፣ የፋሲለደስ፣ የአባጂፋርና ሌሎችንም ውብ የኪነ ሕንጻ ጥበቦችን ሲያኖሩልን፤ የራሳችንን ጥበብ ጨምረን ከዘመኑ ጋር አዋህደን እንድንኖርበት እንጂ፤ የእነሱን ብቻ እያደነቅን፣ ገፋ ሲልም በእነርሱ የጥበብ አሻራ ላይ መግባባት አቅቶን ቅርስ እየተናጠቅን እንድንኖር አይደለም፡፡ በተመሳሳይ ቀለም በጥብጠው ብራና ፍቀው ታሪክና ገድል የከተቡ አያቶቻችን፤ በዘመናዊው ሥነ ጽሑፍ የታገዙ ታሪክ ሰናጅ አባቶቻችንን ተከተውና ሁነቶችን ሰንደው ያኖሩልን፤ ታሪካችንን አውቀን፣ ከታሪካችን ተምረን የተሻለ ታሪክ እንድንሰራ እንጂ በታሪክ እንድንጋደል አልነበረም፡፡

አያት አባቶቻችን በመተማ፣ በመቅደላ፣ በዓድዋ፣ በካራ ማራና ሌሎችም አውደ ውጊያዎች ተዋድቀው የአገራችንን ነጻነት ሲያስጠብቁና እኛንም ከተገዢነት ሲታደጉን፤ የግዛትም፣ የአካልም፣ የሕሊናም ነጻነታችንን አስጠብቀን እንድንዘልቅ፤ በነጻ አስበን፣ በነጻነት የምንፈጽምበት አገርና ሰብዕና እንዲኖረን፤ የሌሎች የሃሳብ ጭነት ማራገፊያ ሳንሆን የራሳችንን ከፍታ አውቀን በራሳችን የምንመራ ባለ ሕሊናና ባለ አዕምሮዎች እንድንሆን ነው፡፡ ይሁንና አሁን አሁን በአንዳንድ ቦታዎች ይሄን ማድረግ ሳይቻልና ይልቁንም እዚህ ግባ በማይባሉ ጉዳዮች ግጭት ሲፈጠርና የሰው ሕይወት ሲያልፍና ንብረት ሲወድም ይታያል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፤ የዛሬው ማንነታችን የአባቶቻችን ፍሬ፣ የመስዋዕትነት ምንዳ መሆኑን ተዘንግቶ፤ ከፍቅርና መተሳሰብ ይልቅ ጥላቻና ቂም፤ ከወንድማማችነትና መደጋገፍ ይልቅ፣ ጠላትነትና መገፋፋትን፤ በመቻቻል አብሮ ከመኖርና ተባብሮ ከመቆም ይልቅ በጥላቻ ስሜት ተቃኝቶ መጠላለፍን ለመዝራት ጥቂት እኩይ ግለሰቦች ሲባዝኑና አውቀውም ይሁን ሳያውቁ አንዳንዶች የዚህ ሴራ ሰለባ ሲሆኑ ተስተውሏል፡፡

በዚህም የሃር ጠላቶች ትናትን አገርን ለቅኝ ግዛታቸው፤ ሕዝብን ለባርነት አገልጋይነት አጭተው ድንበር ደፍረው የዘለቁ ጠላቶች እሳቤና መንፈስ አራማጅ ሲሆኑ፤ ወንድማችንን ከማቀፍ ይልቅ መገፋትና ማፈናቀልን፣ ሲታመም ከጎኑ ሆነን ከማጽናናትና ለምህረት እጃችንን ከመዘርጋት ይልቅ ለመግደል እጃቸውን ማንሳትን፣ ለአብሮነታችን ዋጋ ከመክፈል ይልቅ ለመለያየታችን እንቅልፍ አጥተው መስራትን ሲመርጡና ለዚሁ እኩይ ተግባር ሲታትሩ እየተመለከትንም ነው፡፡ ይህ ደግሞ አባቶቻችን ዋጋ ከከፈሉንን ሕልም የራቀ፤ ከኢትዮጵያዊነታችን ከፍታ የወረደ፤ ከሰብዓዊነታችን እሴት የተፋታ፤ ከታሪክ ስሪታችን የተቃረነ፣ በጥቅሉ ቀደምቶቻችን ለምን ዋጋ እንደከፈሉንን ያልተገነዘበ ድርጊት ነው፡፡

ዛሬ ትልቅ ቦታ ሰጥተነው የምንውለውና ለማክበርም አደባባይ የምንወጣለት የአርበኞች የድል ቀን፤ በዓድዋ የመከነውን ቅኝ ገዢዎች የአባቶቻቸውን ሕልም እውን ለማድረግ በልጆቻቸው የተዘመተብንን የወረራ ተግባር የአባቶቻቸው ልጅ የሆኑት ኢትዮጵያውያን አርበኞች ዳግም ድል በማድረጋቸው ነው፡፡ እነሱ የተከፈላለቸውን ዋጋ ሳይዘነጉ ባለህልም ሆነው በዘመናቸው የሚፈለግባቸውን ዋጋ ከፍለው ነጻዋን አገር አስረከቡን፡፡

እኛ ደግሞ ይሄን የአባትን አደራ እና የመስዋዕትነት ዋጋን መዘንጋታችን ዋጋ እያስከፈለን፤ በሃይማኖታዊ ጉዳዮቻችን ሳይቀር ከፈጣሪ የተሰጠንን የሰላምና አብሮነታችንን ጉዳይ ጭምር እያጠለሸን እንገኛለን፡፡ በመሆኑም እንዲህ እንደ ሚያዝያ 27 ያሉ የድል ቀኖችን ስናስብ፤ አባቶቻችን አንድ ላይ የሞቱት እኛ በፍቅርና በአንድነት እንድንኖር እንጂ፤ አብሮነታችንን አጥፍተን እየተገፋፋንና እየተጠፋፋን እንድንኖር አለመሆኑን በመገንዘብ ሊሆንና በወዳጅትና አንድነት መንፈስ አገራችንን ልንታደግ ይገባል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## “የ‘ኛ ፖለቲካ...”

ግርማ መንግሥቴ

ይሄ “የ’ኛ” የሚባል ነገር ጉድ እያፈላ ነው። በአዋጅ “የ’ኛ” የሚለው ቀርቶ በ”የ’ኔ” የተተካ እስኪመስል ድረስ “የ’ኛ” የሚለው አደጋ ላይ ወድቋል። ችግሩ “የ’ኔ” እና “የ’ኛ” ተቃርኖ መኖር ብቻ አይደለም፤ ችግሩ ሌሎችም መኖራቸው ነው። ለምሳሌ “መጤ”፣ “ነባር” አይነት ዳይኮቶሚዎች። እነዚህን የቀፈቀፈውም የዘመኑ ፖለቲካችን ነው። ለጉዳያችን መግቢያ “የ’ኛ ፖለቲካ” ብለን ስንነሳ፣ የፈጠራ መብት ባለቤትነትን ስለ ማስከበር ልናወራ ወይም፣ የራሳችን የሆነ ያለን ስለመሆኑ ለመደስኮርም አይደለም። ይልቁንም፣ ሁሌም ወደኋላ የሆነውን ጉዟችንን በተመለከተ፣ የአሁኑ ዘመን ፖለቲካ፣ ፖለቲከኞቻችንን መሬት ላይ ያለውን የእነዚህ ሁለቱን ድርብ ውጤት በተመለከተ ጥቂት ለማለት ነው።

“የ’ኛ ፖለቲካ” ስንል መርህ አለው ወይስ የለውም፤ የሚከተለው ርእዮት አለው ወይስ የለውም፤ የቆመበት መሰረትስ ቢሆን ምንድን ነው? የሚሉትን “ቀላል፣ ቀላል” ጥያቄዎች ለመመርመር፤ መርምሮም ምላሽ ለማግኘት አይደለም። ወይም፣ ፖለቲካችን እንደ ሩሲያ ኮሚኒስት ነው፤ አይ፣ እንደ ቻይናው መሰረቱን ኮንፊሺየስ ላይ የገነባ ኮሚኒስት ነው፤ አይደለም፣ እንደ ጀርመኑ ደሀን ማእከል ያደረገ የሶሻል ዲሞክራሲ ርእዮት አራማጅ ነው፣ ወዘተርፈ ... እያልን አንድ የፖለቲካ ማንነት ላይ ልናቆመው፤ ያለ ባህርይው ልናስጨንቀው እና የሌለውን ልንሰጠው አይደለም።

“የ’ኛ ፖለቲካ” ያለበትን ሁኔታ፣ እየሆነ፣ እያደረገ ያለውን ተግባር፤ በተከታዮቹ ዘንድም ይሁን ሌሎች እያስረፀ ያለውን አመክንዮ (ከተባለ)ለማሳየት፤ እንደ ዜጋ መሬት ላይ ያለውን እውነት መሰረት አድርገን ለማሄስ ነው። የእኛን ፖለቲካ በተመለከተ ብዙ ተብሏል። ተደግፏል፤ ተነቅፏልም። ይሁን እንጂ፣ በአብዛኛው ለወገነው ያደላ አስተያየት ነው ሲዘንብ የኖረ እንደመሆኑ ሲስተካከል አይታይም። አለመስተካከሉንም ከመብት ጥሰት በመጀመር ልናየው እንችላለን።

“የ’ኛ ፖለቲካ” የሰዎችን መብት ያከብራል ወይ ብሎ በመጠየቅ ጉዳዩን መጀመር ይቻላል። “አያከብርም” ካልን ማሳያዎቹ ብዙ ናቸውና እዳው ገብስ ነው ማለት ነው። ከላይ በመግቢያ አንቀፃችን ላይ ለመጠቋቆም እንደሞከርነው፣ አግላይ አስተሳሰቦች (እኔ#እነሱ፤ መጤ#ነባር ...) ወደ አገራችን የተጋዙት(ኢምፖርት የተደረጉት) በፖለቲካ ፓርቲዎቻችን አማካኝነት ነው። አገራችን አለም ጉድ እስኪል ድረስ በመቶዎች የሚቆጠሩ፣ በብሔር ፖለቲካ (ያው “እኛ” ሳይሆን “እኔ” ማለት ነው) ላይ የተመሰረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ አሸን የፈሉባት ምድር ነች።

ይህ ሁሉ ይሆን ዘንድ በሩን የከፈተው የድህረ 1983 ዓ.ም “ዲሞክራሲን ያለገደብ” የተባለለት ወቅት ሲሆን፤ ያንን ተከትሎ ባልተጠበቀ ፍጥነት ቁጥራቸው መቶን የዘለለው ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን (በወቅቱ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት 111 መድረሳቸውን በአመታዊ ሪፖርቱ አስታውቆ ነበር) ዛሬም ድረስ ከ30 ምናምን አመት በኋላም ከብሄር የተላቀቀ አስተሳሰብ ብቅ ሊል አልቻለም። ለአገርና ሕዝብም ከመጠላለፍ፣ መገፋፋትና ከሴራ የተላቀቀ የፖለቲካ አስተሳሰብ ሊያገኙ አልቻሉም።

“የ’ኛ ፖለቲካ” አንድ ሰው መስማት ያልፈለገውን እንዳይሰማ፤ መስማት የሚፈልገውን እንዲሰማ ምንም አይነት እድል አይሰጥም፤ አፋኝ ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ፖለቲካን መስማት እማይፈልጉ ሰዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። እነሱ አይፈልጉ እንጂ ዙሪያቸውን የከበባቸው ብሔርንና መሰል ጉዳዮችን መሰረት ያደረጉ ነገሮች ናቸው። አልሰማም ቢሉ እንኳን አለመስማት አይችሉም። በሌላው ዓለም ቢሆን አንድ ሰው ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ መስማት የማይፈልገውን ያለ መስማት መብቱ የተጠበቀ ነው። “የ’ኛ ፖለቲካ” ግን ይህንን አይፈቅድም። ካልሰማነው ይፈርጀናል። “የ’ኛ ፖለቲካ” እስካሁን ያመጣው፣ ሕዝብም ከ’ሱ ያተረፈው ነገር ቢኖር የእርስ በርስ ግጭትን ነው።

“የ’ኛ ፖለቲካ” ያስተማረን ቃላት (ቮካቡላሪስ) ቢኖሩ “መጨፍጨፍ”፣ “ጭፍጨፋ”፣ “ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ...”፣ “ኢሰብአዊነት በጎደለው ...” የሚሉት ናቸው። በቀን በቀን በጆሮቻችን በመንቆርቆራቸው ምክንያት ለምደናቸው አርፈናል። ይህ ሁሉ እንግዲህ “የ’ኛ ፖለቲካ” ውጤት ነው። “የ’ኛ ፖለቲካ” ሲያስፈልገው አገርና ሕዝቡን ሁሉ ይክዳል። ይክድና ከባእድና ባንዳ ጋር ይወግናል። ይህ ጋብቻውም አገር በሰላም ውላ በሰላም እንዳታድር አድርጎ ዜጎችን ለሰላም እጦትና ሕይወት ማጣት ይዳርጋል። ከእኛ ፖለቲካ እያየን ያለነው ይህንን ነው።

ከ”የ’ኛ ፖለቲካ” ተዋንያን አገራዊ አጀንዳ ያለው የሚመስለው በጣት የሚቆጠረው ነው። ሁሌም ክርክሩም ሆነ ውዝግቡ ነጠላ ጉዳይ ላይ ነው። ሁሌም አጀንዳ ሲመዝ አንዱን ወገን አስደስቶ፤ ሌላኛውን አሳዝኖ፤ አንዱን ባንዱ ላይ ሊያነሳሳ በሚችል መልኩ እንጂ ሕዝብን የሚያሳትፍ፤ “እኛ”ን መሰረት ያደረገ አይደለም። አግላይ ነው። አንዳንዴ ይህ ተግባሩ “አቃፊነት እርሜ”፣ “አቃፊነት ለምኔ” ያለ ሁሉ ያስመስልበታል። “የ’ኛ ፖለቲካ” በዚህ ሲሉት በዚያ ነው። “አገራዊ ፖሊሲህስ?” ሲሉት፤ “እሱን አሁን አይደለም፤ ከመረጣችሁኝ በኋላ አቀርባለሁ” የሚል መልስ የሚሰጥ አላጋጭ ነው።

“የ’ኛ ፖለቲካ” አመሉ ብዙ ሲሆን፤ “ንትርክ ውስጤ ነው” ያለ ይመስል፤ ሁሌም ንትርክ፣ ሁሌም ውዝግብ ሁሌም .... ነው። ሥልጣንን እየፈለገ ገዢውን ፓርቲ ሥልጣን ላይ ሙጭጭ አለ ይላል፤ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚሆን አንድ ጡብ ሳያስቀምጥ ዲሞክራሲ የለም ይላል፤ ስለ ሰላም ሳያስተምር ሕዝብ ሲጋጭ ሲያይ ሕዝቡን ጨረሰው ይላል፣....። እውነታው ግን የእርቀ ሰላም ኮሚሽን በየክልሎችና ክልል ከተሞች በመዘዋወር ከሕዝቡ ጋር በመወያየት ያረጋገጠውና በሚዲያ ይፋ ያደረገው (በወቅቱ የኮሚሽኑ ምክትል ሊቀመንበር የትነበርሽ ንጉሴ እንደተናገሩት) ሲሆን፤ እሱም “በእኛ መካከል፣ በሕዝቡ መካከል ምንም ችግር የለም። እኛ ሁሌም አንድ ነን። እኛን የሚያጫርሱን ፖለቲከኞች ናቸው። እነሱ ካረፉ ሰላም ይሆናል።” የሚል ነበር። (በወቅቱ “የኢትዮጵያ እርቀ ሰላም ኮሚሽን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተፈጠሩ 21 ግጭቶችን እያጠና መሆኑን በሚል ቀርቦ የነበረን ዜና ያስታውሷል።)

“የ’ኛ ፖለቲካ” ራስ ወዳድ ነው። ማእከል አድርጎ የሚንቀሳቀሰው ሕዝብንና አገርን ሳይሆን እራሱንና እራሱን ብቻ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ያለንበት የከፋ የእርስ በርስ ጦርነትና ያስከተለው ሰብዓዊ ቀውስና ኢኮኖሚያዊ ውድመት ባልተከሰተም ነበር። “የ’ኛ ፖለቲካ” ጨካኝ ነው። አሁን በአገራችን ላይ እየደረሰ ያለውና ይደርሳል ተብሎ የሚሰጋውም ሆነ የሕዝብ መጨነቅ፤ ማዘን፤ መማረር፣... ምንም አይመስለውም። ይህ ሁሉ እሳት ሲነድ እናጥፋው ያለ ፖለቲከኛ ማግኘት አልተቻለም። ለዚህም ይመስላል አንዲት እናት “የዘንድሮ ፖለቲከኛ ብዛት እንጂ ጥራት የለውም” አሉ እየተባለ ሲነገር የነበረው።

“የ’ኛ ፖለቲካ” ደም ማፋሰስ እጣ ክፍሉ ነው፤ ዜጎችን ወደ ግጭትና እርስ በእርስ ጦርነት ማሰማራት የኑሮ ዘዴው ነው፤ የዜጎችን፣ በተለይም ወጣቱን በማህበራዊ ሚዲያ ማደንዘዝ የህልውናው ጉዳይ ነው፤ ስልጣን ጥሙ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ከዚህ የፀዳና በትክክልም “የ’ኛ ፖለቲካ” የሚሉት የፖለቲካ ስሪት ያስፈልጋቸዋል።

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

# እንደገና አፈርሁ፤ መሸሸጊያ- መደበቂያ አጣሁ... !?

ሁለት አስርት አመታትን በተሻገረው የጋዜጠኝነትና የሕዝብ ግንኙነት ሙያዬ እንዳለፉት አራት አመታት በእጅጉ ተፈትኖ አያውቀውም። ለአገራችን ብዙኃን መገናኛዎችም እንደነዚህ አራት አመታት ያለ ፈተና ገጥሟቸው አያውቅም። በተለይ ሙያዊ ስነ ምግባራቸው አክብረው የሚሰሩ ሚዲያዎች በየዕለቱ የቱን መረጃ እንዴትና መቼ እንደሚዘግቡት በአርትኦት ኮሚቴ ስብሰባዎቻቸው መዋዘገባቸው የማይቀር ሆኖ ይሰማኛል። በተለይ የአዲስ ዘመንና የሪፖርተር ጋዜጦች ርዕሰ አንቀጽ ጸሐፍት ላይ ፈተናው የከፋ ነው። እኔም ለዛሬ የ"አዲስ ዘመን"፤ የ"ነጻ ሀሳብ" እየተሰናዳሁበት የነበረው አጀንዳ "ፖለቲካዊ መቤዠት" የሚል ነበር። ሆኖም በጎንደር፣ በስልጢ ዞን ወራቤ፣ በአዲስ አበባ በዓርቡ የመጨረሻ የጎዳና አፍጥር፤ በእለተ ኢድ አልፈጥር ደግሞ ደረጃው ቢለያይም በድሬዳዋና በሁሉም ክልሎች የተስተዋሉ ነውረኛ፣ አደገኛና አሳፋሪ አዝማሚያዎች የእጄን አጀንዳ አስጥለው በሰሞነኛ ጉዳዮች ላይ እንድጽፍና ወደኋላ ተመልሼ መጣጥፎቼን እንድቀራርም አስገድደውኛል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በከብቶች በረት ከተወለደበት ሰዓት ጀምሮ ለሰው ልጅ ድኅነት ሲል ከመሰደድ እስከ ሞት፤ ጽኑ መከራና ስቃይን ተቀብሏል። በተለይ በመጨረሻው ሰዓት ከሰው ልጅ አዕምሮ በላይ የሆነ ስቃይ ፣ መከራ ፣ እንግልትና ግርፋትን ተቀብሎ ፤ በጲላጦስ ከወንበዴዎች ጋር ተፈርዶበት ፤ በቀራንዮ አደባባይ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ፤ ነፍሱን በፈቃዱ ሰጥቶ አዳምንና ዘሩን ከሞት ወደ ሕይወት ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ፣ ከባርነት ወደ ነፃነት መልሶ በሦስተኛው ቀን መቃብር ክፈቱልኝ ፣ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ፤ በማቴ 28፥5 ላይ "እነሆም የጌታ መልአክ ከሰማይ ወረደ፣ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፣ እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና። እንደተናገረው ተነስቷልና በዚህ የለም ኑና እዩ አላቸው።" ተብሎ እንደተገለጸው፤ ብርሃንን ተጎናጽፎ በታላቅ ኃይልና ስልጣን በክብር ተነስቷል። በዚህ ታላቅና የክርስትና ራስ በሆነው የትንሳኤ ሰሞን ነው በጎንደር ለዛውም 44ቱ ታቦት ቅድስት ከተማ እየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ህያው ያደረገውና በአምሳሉ የፈጠረው ሰው በወገኑ የተገደለው። በዚህ ያላፈርን ፣ ያላጠርንና መደበቂያ ያላጣን በምን እናፍራለን!?

ረመዳን በእስላማዊ ቀን አቆጣጠር ቅዱስ ቁራን ለነብዩ ሙሐመድ የተገለጠበት የተቀደሰ ዘጠነኛ ወር ነው። ከእስልምና አምስቱ አምዶች አንዱ የሆነው ጾም የሚያዝበት የተቀደሰ ወር ነው። የጀነት በር የሚከፈትበት፤ የጀሀነም ደጆች የሚጠረቀሙበት ልዩ ወር ነው። ጾም ከተፈታ በኋላ ያሉ ሶስት ተከታታይ ቀናት ወይም ሻዋል እንዲሁ የተባረኩ ናቸው። በዚህ ታላቅ ወር ነው በአዲስ አበባም በወራቤም አሳፋሪ ነውር ያየነው። ያ ልዩነት አንገታችንን የደፋነው ። "ከኢድ እስከ ኢድ ወደ አገር ቤት፤" ብለን ከመላው ዓለም እንግዳ ጠርተን በኢትዮጵያዊ ወግና ማዕረግ በክብር አስተናግደን መመለስ ሲገባን ያሳዘናቸው። እምነታችንን እንደማንኖረው ገመናችን የተጋለጠው። እርቃን የቀረው። በሁለቱም እምነቶች ያዋረዱን ጥቂቶቹ ቢሆኑም ሁላችንም በአንድም በሌላ በኩል ከደሙ ንጹሕ አይደለንም።

በእነዚህ ሰሞነኛ አገራዊ ነውሮች እንደገና ለማፈር፣ ለማጠርና መደበቂያ ለማጣት የግድ የጥቂት ግፈኞችን ማንነት መጋራት አያስፈልግም። የተገኙበትን ብሔርም ሆነ ሃይማኖት ስለማይወክሉ። በግሌ እንደ አንድ

> **በ**ባህላዊ ወረቶቻችንንም (cultural capitals) ሆነ ዕምነቶቻችንን የትውልዱን ሰብዕና ማነፅ፣ ምግባሩን መግራት እንዲችሉ ራሳቸውን መፈተሽ፤ ስለ አገልግሎታቸው ስነ ዘዴ ቆም ብሎ ማሰብ ማንሰላሰል ወቅታዊ ጥሪ ሊሆን ይገባል፡፡ ባህላዊም ሆኑ ሃይማኖታዊ ትእምርቶቻችን የትውልዱን ሰብዕና ላይ ላዩን የሚቀባቡ ሳይሆን ከውስጥ ወደ ውጭ የሚያንፁ፤ የአስተሳሰብ ልዕልናን የሚያቀዳጁ ሆነው እንዲያገለግሉ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል

ኢትዮጵያዊ ዜጋም እንደ አፍሪካዊም በሀፍረት አንገቴን ደፍቻለሁ። ከፍ ሲልም እንደ ሰው ቅስሜ ተሰብሯል። ሕመሙ አጥንቴን ዘልቆ ተሰምቶኛል። እንደ እግር እሳት ዕለት ዕለት ይለበልበኛል። ሆኖም ከእኔ ሕመም ስቃይና ሀፍረት በላይ የክልሉ ሕዝብ፣ መሪው ፓርቲ፣ ተፎካካሪዎችና አክቲቪስቶች በተፈፀመው አረመኔአዊ ድርጊት ይበልጥ አፍረዋል፤ ተዋርደዋል ብዬ አምናለሁ። ያላፈረ ቢኖር እሱ ሰውነቱን ይጠራጠር።

በጎንደር የሆነው ያሳፈረንንና ያሳዘነንን ያህል። የአዲስ አበባውና የወራቤው ያለ ልዩነት አሳፍሮናል። በሰማዕታት ሀውልት ላይ፣ በአብያተ ክርስቲያናት ላይ፣ በመስጅዶች ፣ በዜጎችና በአገር ሀብትና ንብረት ላይ የጥፋት እጅ የሚያስነሳ ምን አይነት ሃይማኖታዊ ቀናዒ ነው !? በድሬዳዋና በሌሎች ክልሎችም የተስተዋሉ እኩይ ድርጊቶች አንገታችንን አስደፍተውናል። ይሄን ስል የሀፍረት ደረጃን ለማውጣት ወይም ሒሳብ ለመተሳሰብ አይደለም። መጠኑ ይነስም ይብዛም የእኔም ሆነ የእነሱ ሀፍረት አንድ ቦታ ላይ ይገናኛል ለማለት እንጂ። የሰሞኑን ኃፍረት ፣ ውርደት የሁላችንም ነው። የሀፍረታችን ፣ የውርደታችን ፣ የቅሌታችንና የነውራችን መጠን ይለያይ ይሆናል እንጂ እንደ ሕዝብ እንደአገር ሁላችንም ከሰውነት ተራ ወጥተናል፤ ጎለናል ፡፡

ጣት መቀሳሰሩና ታርጋ መለጣጠፉ ጊዜያዊ ፖለቲካዊ ነጥብ ከማስቆጠር አንጻር ጥቅም ሊኖረው ይችላል። ይህ ግን ለአገርም ሆነ ለሕዝብ አይበጅም። ዘላቂ መፍትሔን አያመጣም። አሁን እሳት ከማጥፋትና ከዘመቻ ስራ ወጥተን ስትራቴጂካዊ መፍትሔ ላይ ማተኮር አለብን። ለመሆኑ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ መልሰን መላልሰን ለተንደረደርንባቸው የውርደት ቁልቁለቶች መግፍኤዎች ምንድናቸው!? ገለልተኛና ከስሜታዊነት የነፃ ተቋም (ለዛውም ካለን) በቀጣይ በጥናት የሚደርስበት ሆኖ ከዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች አራቱን እንደሚከተለው አነሳለሁ።

**1ኛ . ትንትናችን በስሜት የተቃኘ መሆኑ፦**

የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/ መስራች አባል አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ በዚያ ሰሞን "አርትስ" ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው "ትላንትም ሆነ ዛሬ እንደ አገር እንደ ሕዝብ የገጠሙንን ፈተናዎች ለመሻገር ሳይንሳዊ ጥልቅ ትንተና ያስፈልጋል። ትንተናው ግን በግዕብታዊነትና በስሜት ሊሆን አይገባም፡፡" ብለው ነበር። ዛሬ ለምንገኝበት ውርክብ የዳረገን የ60ዎቹ ትውልድም ሆነ እሱን ተከትለው የተቀፈቀፉ ነፃ አውጭ ፓርቲዎች በስሜትና በደም ፍላት ተመስርቶ የተደረገ ትንተናና የደረሰቡት የተሳሳተ ድምዳሜ ነው ማለት ይቻላል። በተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ተንጠልጥሎ የሚሰጥ የመፍትሔ ርዕዮተ ዓለምም ሆነ ለውጥ ውጤቱ ከድጡ ወደ ማጡ ነው፡፡

የመደብ ትግልን በማንነት ጥያቄ አሳክሮ የተወጠነው ዘውጌ'ዊ ፌደራሊዝምም ሆነ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከተዘፈቅንበት አዘቅት ሊያወጣን ይቅርና ለከፋ ዘርፈ ብዙ ቀውስ ዳርጎን አርፎታል። ካርል ማርክስ " ታሪክ ራሱን ሲደግም መጀመሪያ በአሳዛኝ ሁኔታ በማስከተል በአስቂኝ ሁኔታ" ያለው እንዳይሆን አበክሮ ማስተዋል ይጠይቃል። እንደ አገር የገጠሙንን ሰሞነኛ ችግሮች በስሜታዊነት ሳይሆን በሰከነ መንፈስ እና ከፓርቲ አጀንዳ ይልቅ አገርን በማስቀደም ቁጭ ብሎ መተንተንና ሀቀኛ ድምዳሜ ላይ መድረስና የመሻገሪያ ድልድይ መገንባት ያሻል ፡፡

**2ኛ. ለችግሮቻችን አገረኛ መፍትሔ አለመሻታችን፦**

ላለፉት 50 ዓመታት እንደ መስኖ ውሃ እነ ሌኒን፣ ስታሊን ፣ ማርክስ ፣ ኤንግልስ ፣ ማኦ ፣ ማኪያቬሊ ፣ ወዘተ . በቀደዱልን የርዕዮተ ዓለም ቦይ መፍሰሳችን አልያም ሲገድቡን መገደባችን ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። ሆኖም ከግማሽ ክፍለ ዘመን በኋላ ዛሬም ጥያቄዎቻችን አለመመለሳቸው ችግሮቻችን አለመፈታታቸው ሳያንስ ይበልጥ ተወሳስበው ውላቸው ጠፍቷል። ለዚህ ነው ለአንደኛው ችግር መፍትሔ ስናበጅ ሌላው እንደ እንቧይ ካብ ከጎን የሚናደው። ከሌኒን ኮርጀን የብሔር ጥያቄን እንደፈታን ስናስመስል አገራዊ ሕልውና አደጋ ላይ የወደቀው። ከሶቪየት ገልብጠን የዕዝ ኢኮኖሚን ስንተገብር ፈጠራ የኮሰመነው ኢኮኖሚ የደቀቀው። ከደቡብ ኮሪያ፣ ከጃፓንና ከቻይና እንዳለ ቀድተን ልማታዊ መንግስት ስናነብር አገር የጥቂቶች ሲሳይ ሆና ያረፈችው፡፡

ለነገሩ ጠንካራ አገራዊ አንድነትና ተቋማት በሌሉበት ልማታዊ መንግስት አይታሰብም። እነዚህ ማሳያዎች ችግሮቻችንን በተናጠል እና በተኮረጀ ርዕዮተ ዓለም ወይም ፖሊሲ ለመፍታት ያደረግነው ሙከራ መክሸፉን ያሳጣሉ። ለዚህ ነው አገር በቀል ወደ ሆነና ዙሪያ መለስ እይታ ማተኮር የሚያስፈልገው። ለዚህ ነው የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር "መደመር" ቁጥራቸው ቀላል ባልሆነ ልሒቃን አገርን ፣ ትውልድንና ዘመንን የዋጀ ምላሽ ተደርጎ የተወሰደው። ፅንሰ ሀሳቡ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፣ በ"ቲንክ ታንክስ" ፣ በሙያ ማህበራት ፣ በዓለም አቀፍ የጥናትና ምርምር ተቋማት ፣ ወዘተ . ሲተች ሲሔስ ደግሞ ይበልጥ የጋራ አካፋይ ሆኖ ሊወጣ ይችላል በሚል ዕምነት፡፡

**3ኛ. የተረኮቻችን ምርኮኛ መሆናችን፦**

ሰለሞን ሥዩም የተባሉ ፀሐፊ በፍ-ት-ሕ መፅሔት ከአንድ አመት በፊት ባስነበቡ መጣጥፍ ታሪካችን ሶስት የትርክት ዘውጎችን መፍጠሩን ፕሮፌሰር ተሻለ ጥበቡን ጠቅሰው ሞግተዋል። አክሱማዊ ፣ ሴም አሪየንታላዊ እና ስር-ነቀላዊ ናቸው። ሶስተኛው የስድሳዎቹ ትውልድ የፈጠረው ነው። የታሪኩንም የፖለቲካውን ትርክት ከስሩ ለመቀየር ነው የሰራው። ትርክት ቀድሞ በተቀመጠ ድምዳሜና ብያኔ ላይ የሚዋቀር መሆኑ የውርክቡ መግፍኤ ነው። የዚህ ትውልድ ቅርሻ የሆኑ "ነፃነትን የማያውቁ ነፃ አውጭዎች" በተለይ ባለፉት 27 አመታት ታሪክን በሸውራራ ትርክት ለመቀየር ያደረጉት ጥረት በተወሰነ ደረጃ ተሳክቶላቸው ነበር ማለት ይቻላል ፡፡

በእነዚህ የፈጠራ ትርክቶች በዜጎች መካከል ጥላቻን ፣ መጠራጠርንና ልዩነትን ጎንቁለው ማሳደግ ችለዋል። በተዛባ ትርክት ለቆሙ የጥላቻ ጣኦታት እንድንሰግድ መስዋዕት እንድንገብር አድርገዋል። ላለፉት በርካታ አመታት በተለይ ለውጡ ከባተ ወዲህ ሰሞነኛውን ጨምሮ የተስፋዋን ምድር ወደ አኬልዳማ ቀይረው ዳግም ቅስማችንን ሰብረው አንገታችንን አስደፍተውናል። ሆኖም ዛሬም ከዚህ የጥላቻ አዙሪት ለመውጣት ተረካችንን እንደገና መበየን እና ቂም በቀል የሚያወርሱ ጣኦቶቻችንን ከአእምሮ ጓዳችን አውጥተን ማንከባለል በየከተሞች ያቆምናቸውን የጥላቻ ሀውልቶች እንደገና ስለፍቅር ስለይቅርታ መቅረፅ አለብን ከዚህ ጎን ለጎን የሕግ የበላይነትን ሳይሸራረፍ የማረጋገጥ ግዴታም አለብን ፡፡

**4ኛ. ከውስጥ ወደ ውጭ ማነፅ፦**

ለዘመናት ዕርቅን ፣ ፍቅርን ፣ ሰላምን ፣ ይቅርታን፣ አንድነትንና ፈሪሀ ፈጣሪን በአደባባይ የሚሰብኩ ወካይ የሆኑ ቱባ ቱባ ባህሎችና ሃይማኖቶች ባሉበት እንዲሁም ከሕዝቡ አብዛኛው ሃይማኖተኛ በሆነበት አገር ሰሞነኛውን አይነት አረመኔአዊ ግፎች መልሰው መላልሰው የሚጎበኙን ለምን እንደሆነ ግራ ያጋባል። መስቀልን ፣ ኢ-ሬቻን ፣ ፍቼ ጨምበለላንና ኢድ አልአደሀን በአደባባይ ባከበርንበት ልክ መገኘት ለምን እንደተሳነን ያስቆዝማል። ለዚህ ውድቀት ላለፉት 50 አመታት የመጣንበት ፖለቲካዊ ሀዲድ የራሱ አስተዋጽኦ ቢኖረውም፤ ሃይማኖታዊ ተቋማት የሚሰብኩንን ሆነው አለመገኘታቸው ለደረስንበት የሞራል ዝቅጠትና ጉስቁልና ሌላዊ ምክንያት ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ በባህላዊ ወረቶቻችንንም (cultural capitals) ሆነ ዕምነቶቻችንን የትውልዱን ሰብዕና ማነፅ፣ ምግባሩን መግራት እንዲችሉ ራሳቸውን መፈተሽ፤ ስለ አገልግሎታቸው ስነ ዘዴ ቆም ብሎ ማሰብ ማንሰላሰል ወቅታዊ ጥሪ ሊሆን ይገባል። ባህላዊም ሆኑ ሃይማኖታዊ ትእምርቶቻችን የትውልዱን ሰብዕና ላይ ላዩን የሚቀባቡ ሳይሆን ከውስጥ ወደ ውጭ የሚያንፁ፤ የአስተሳሰብ ልዕልናን የሚያቀዳጁ ሆነው እንዲያገለግሉ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

**ልዑል አምላክ ልብ ይስጠን ! መውጫውን ይግለጥልን ! አሜን።**

# ወቅታዊ

# ‹‹ አመራሩም ሆነ ባለሙያው የተጣለበትን የሕዝብ አደራ በአግባቡ የማይወጣ ከሆነ ሌብነትን ማስቆምና መቅጣት ያስፈልጋል››

- አቶ ክርስቲያን ታደለ
የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

**ምህረት ሞገስ**

6ኛው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተቋቋመ እንሆ አንድ ዓመት ሊሆነው ጥቂት ጊዜያት ቀርተውታል። ህዝቡ አገር አቀፍ ምርጫውን ተከትሎ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የተወሰኑም ቢሆኑ ከሌሎች ፓርቲዎች ወንበር ያገኙ በመኖራቸው የሞቀ ክርክር ይሠማል። በአገሪቱም የተሻለ ሠላም እና ደህንነት፤ የአገር ዕድገት እና የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሁኔታ እንደሚኖር ተስፋ ተጥሎ ቆይቷል። አዲሱ ምክር ቤት ከቀደሙት በተሻለ መልኩ አስፈፃሚዎችን ይቆጣጠራል፤ ሚናውንም ይወጣል የሚል እምነትም ነበር። ለመሆኑ 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚጠበቅበትን ሚና እየተወጣ ነው? በማለት ከአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ተወክለው የምክር ቤት ወንበር ያገኙትን እና የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑትን አቶ ክርስቲያን ታደለን አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበናል።


**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ቀደም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚናን በአግባቡ እየተወጣ አይደለም በሚል ሲተች እንደነበር የሚታወስ ነው። በእርሶ ግምገማ የአሁኑ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚና እንዴት አገኙት?**

**አቶ ክርስቲያን፡-** ያላደጉ አገራት መልካም ያልሆነ አንዱ ተሞክሮ ያለፈ ነገርን መውቀስ ነው። ያለፈው ምክር ቤትን ለመተቸት ይሔን ሰርቷል አልሰራም ለማለት ምክር ቤቱ ይሠራቸው የነበሩ ሥራዎችን በጥልቀት ማየት እና መፈተሽ ያስፈልጋል። እንደአገር የነበርንበትን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አውዶችን መረዳት እና መገምገም የተገባ ነው። በዚህ ረገድ ባለፈው የምክር ቤት ዘመን የነበሩ እና አሁንም የምክር ቤት አባል የሆኑት በዚህ ላይ ሃሳብ ለመስጠት የተሻሉ ናቸው። ስለዚህ እኔ ስላለፈው ሳይሆን ስለአሁኑ መናገር ምቾት ይሰጠኛል።

የአሁኑ ምክር ቤት በአንፃራዊነት የተማሩ ሰዎች ማለትም ከምክር ቤት ውጪ ኑሯቸውን ለመምራት አቅምም ብቃትም ያላቸው ሁሉም ባይሆን እንኳ የተወሰኑት የምክር ቤት አባላት ከፖለቲካ ዝንባሌያቸው ባለፈ በምሁርነታቸው በአደባባይ የተመሰከረላቸው እና እንደግለሰብ ለኢትዮጵያ እና ለልጆቿ ባላቸው ቀናይ ሃሳብ የሚደነቁ ናቸው። ይህ ሲታይ የ6ኛው ምክር ቤት የመጀመሪያ ዓመት ስለሆነ እስከአሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ሊጠቅሙ የሚችሉ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ረገድ በአንፃራዊነት የተሻለ ተሳትፎ ያላቸው ናቸው ለማለት ያስደፍራል፡፡

የምክር ቤት አባላቱ ከሚወክሉት ፓርቲ ይልቅ ለህዝባቸው እና ለአገራቸው የሚወግኑ መሆኑን መመስከር እችላለሁ። በዚህ አጭር ጊዜ ይህ መልካም ጎን ነው። እርስ በእርስ እንደግለሰብ እንኳን በቂ ትውውቅ ለማድረግ ማን ምን ጠንካራ ጎን አለው የሚለውን ለማየት ጊዜው ገና በመሆኑ የቸኮለ ድምዳሜ ላይ መድረስ እንዳይሆን እንጂ እስከ አሁን ባየሁት የምክር ቤቱን ሥራዎች በሚያቀላጥፉ ቋሚ ኮሚቴዎች አባላት እና የቋሚ ኮሚቴ አመራሮች በህገመንግስቱ እና በምክር ቤት የህዝብ እንደራሴነት የተሰጣቸውን ሃላፊነት በወጉ ሲወጡ እና ለመወጣትም ሲንቀሳቀሱ እያስተዋልኩ ነው።

በጋራ የሥራ አፈፃፀም የምንገመግምበት ሁኔታ ስላለ ሁሉም የተሰጠውን ሃላፊነት ለመወጣት ሲታትር እየታየ ነው። ነገር ግን አገርም ህዝብም ከዚህ ምክር ቤት የተለየ ነገር ይጠብቃል። አንደኛ ላለፉት 30 ዓመታት ሥርዓት እና መዋቅር ሰራሽ በሆነ መንገድ የተለየ ጭቆና እና ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ እንዲሁም ማህበራዊ በአጠቃላይ ሁለንተናዊ በደል ውስጥ እንደነበርን አይዘነጋም። ዜጎች በማንነታቸው ሲጠቁ እና በሚከተሉት ሃይማኖት ተለይተው ሲገፉ እና ሲጨቆኑ ነበር። ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ሲዘራ የነበረው የጥላቻ እና የመከፋፈል ዘር ፍሬ አፍርቶ ዛሬ



ፎቶ ፡- ፀሐይ ንጉሤ

**ጠንካራ ተቋም ያላት አገር ጠንካራ ትሆናለች፡፡ ዜጎች የተቀላጠፈ አገልግሎት ያገኛሉ፡፡ የእኛ ዋነኛ ፍላጎት ያ ነው**

ኢትዮጵያውያንን ክፉኛ እያቃወሰ እንደሆን እያየን ነው። ከዚህ አንፃር ሕዝብም ይህ ምክር ቤት ከተለመደ የምክር ቤት አሠራር ወጣ ብሎ ለአገሩ አርበኛ እንዲሆን ለህዝቡ ፍትህ እና እኩልነት እንዲሁም ሰላም መረጋገጥ ሁነኛ እርምጃ ወስዶ አገርን ከዚህ ከመርገምቱ ጊዜ ወደ ፊት ወደ ብሩህ ተስፋ የማሸጋገር ሃላፊነት እንዳለበት እኔም ይሰማኛል። ህዝብም ይህን ይጠብቃል።

ከህዝብ ተስፋ አንፃር ምን ሥራዎች ተሠሩ ከተባለ መልሴ ገና የመጀመሪያ ዓመት ሥለሆነ ብዙ የሚጠበቅብን ሥራ አለ የሚል ብቻ ነው። ከዚህ በኋላ ሕዝብ እንደራሴ ብሎ አንዴ ልኮናል። ይህንን ተስፋውን ለማረጋገጥ በየጊዜው እንደግለሰብም ሆነ እንደምክር ቤት በሚኖሩ የህዝብ ግንኙነቶች ምን ሠራችሁ ብሎ መጎትጎት እና መደገፍ እንዲሁም ማበረታታት አለበት። ምክር ቤቱ በበኩሉ የአንበሳውን ድርሻ መጫወት አለበት። ምክንያቱም ይህ የእንደራሴዎች ምክር ቤት መላው ኢትዮጵያውያንን የሚወክል ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አስፈፃሚው አካል ሰላምን ደህንነትን ፍትህን እና እኩልነትን ማዕከል አድርጎ እንዲሠራ መከታተል ብቻ ሳይሆን የማዘዝ ስልጣንም ጭምር ያለው ነው። አንዳንድ አካባቢዎች የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የሚፈፀሙ ከሆነ እንዲመረመር እና የፌደራል መንግስት ያንን እንዲያስቆም የማዘዝም ስልጣን ያለው ትልቅ የመንግስት አካል ነው። ከዚህ አንፃር እስከ አሁን በአንድ አመት ውስጥ ጉልህ ሥራዎችን ሠርቷል ማለት ባይቻልም ለቀጣይ ሥራ መደላድል ለመፍጠር የዝግጅት ምዕራፍ ላይ እንደነበር መውሰድ ይቻላል። በዚህ ጊዜ ውስጥ እያንዳንዱ የምክር ቤት አባል ያለው ተሰጥኦ እና አቅም ምን ያህል ነው? ምንስ ውስንነት አለበት? በሚለው ላይ በደንብ ተጠንቶ እንደየመክሊቱ እንደየችሎታው ሁሉም ለአገር ሰላም እና አንድነት ያለውን እንዲያበረክት አሠራርን የመዘርጋት እና ነገሮችን የማመቻቸት ሥራ የሚሠራበት ነበር ብሎ መውሰድ ይቻላል።

በተጨማሪ ምክር ቤቱ ካሉት አራት ተልዕኮዎች ውስጥ አንዱ ህግ የማውጣት ሥራ ነው። አሁንም ህግ በማውጣት ላይ ይገኛል። እንዲሁም አስፈፃሚ አካልን የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት። አሁንም በየጊዜው ህዝብን በፍትሃዊነትና በእኩልነት እያገለገሉ ስለመሆናቸው በመቆጣጠር ላይ ይገኛል። እዚህ ላይ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የታለመለትን ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መንገድ እየሠሩ መሆኑን ያጣራል። እዚህ ላይ ምክር ቤቱ በፌዴራል ሥልጣን እርከን ውስጥ ለሚወድቁት አስፈፃሚዎች ዕቅዳቸውን እንዲከልሱ እስከማዘዝ የደረሰ ስልጣን አለው።

ሌላው የመንግስት በጀት እና ንብረት ለታለመለት ህዝባዊ ዓላማ እየዋለ ስለመሆኑ ይከታተላል። በዚህ ሒደት ክፍተት አለ ብሎ ካመነም እርምጃዎች እንዲወሰዱ ትእዛዝ መስጠት ይችላል። ሌላው የመራጭ ተመራጭ የውክልና ሥራ ነው። በዓመት ሁለት ጊዜ ሁሌም እንደሚደረገው የካቲት እና ሃምሌ ላይ የውክልና ሥራዎች ተሠርተዋል። በተለይም ገዢው ፓርቲ በምርጫ ቅስቀሳው ቃል የገባቸው የልማት ዕቆዶች በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ የተካተቱትን ማለት ነው በተጨባጭ ሕዝብ ጋር ደርሰዋል ወይ? በማለት ሥራዎች የሚሠሩባቸው ከህዝብ ጋር ግንኙነት የሚደረጉባቸው ጊዜያቶች ናቸው።

ከዚህ ባሻገር መራጭ ሕዝቡ የሚያነሳቸው ተጨማሪ የፍትህ፣ የልማት፣ የእኩልነት፣ የመልካም አስተዳደር እና የሠላም ጥያቄዎች ካሉ ከቀበሌ ጀምሮ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል እየተባለ በየደረጃው ወደ ፌዴራል የሚመጡትንም በማቅረብ በተቀናጀ መንገድ የፌዴራል ተቋማት እንዲፈቷቸው አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል። ያም ክትትል የሚደረግበት ነው። ሌላው እስካሁን ተሠርቶ የማያውቅ እና ይሔኛው ምክርቤት በትኩረት እየሠራበት ያለው የህዝብ ዲፕሎማሲ ነው። በእርግጥ ኢትዮጵያ በመደበኛነት የዲፕሎማሲ ሥራ በውጪ ጉዳይ በኩል ትሠራለች። ነገር ግን ይሔ ምክር ቤት በተለያዩ የዓለም ዐቀፍ ምክር ቤቶች ህብረት አባል ነው። ስለዚህ በዛም ሆነ እንደፓርላማ ቡድን ኢትዮጵያ በተለይም አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ከተማ በመሆኗ እዚህ ላሉ አምባሳደሮች እና ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ በማሰማት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘላቂ መብቶች፣ ጥቅሞች እና ዘላቂ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ውሳኔዎች እንዲተላለፉ፤ የኢትዮጵያ ወዳጆች እና አጋሮች እንዲያደርጉ የተለያዩ የማህበረሰብ አባላት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ወኪሎችን መደበኛ በሆነ መልኩ በሰላም እና ውጪ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በኩል እየተሠራ ነው። ነገር ግን እንደየአገሩ ሁኔታ የወዳጅነት ቡድን ተቋቁሞ መሠራት ይኖርበታል። በዚህ በኩል መዘግየት መኖሩ እኔም ይሠማኛል። ወደ ፊት ለኢትዮጵያውያን ጥቅም የሚያስገኙ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ሊሠሩ እንደሚችሉ ተስፋ እናደርጋለን። በቋሚ ኮሚቴዎች እና በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች በኩል በመደበኛነት እየተሠሩ ቢሆንም በተጠናከረ መልኩ መቀጠል አለበት። ነገር ግን ሕዝብ ከሚጠብቀውና ምክር ቤቱ ካለው አቅም አንፃር ግን ገና ብዙ መሥራት የሚገባን ሥራዎች መኖራቸው ይሠማኛል።

**አዲስ ዘመን፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ከማካሔድ ባለፈ አስፈፃሚ ተቋማትን በመገምገም ተጠያቂነትን እስከማስፈን የሚደርስ ስልጣን አለው። በእርግጥ ይህንን ሚናውን እየተወጣ ነው?**

**አቶ ክርስቲያን፡-** አዎ! እንደአብነት ልጥቀሰው

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



የኦዲት ግኝቶች በተለይ የክዋኔ ኦዲት ላይ ያሉት የንብረት ብልሽቶች አስደንጋጭ ናቸው፡፡ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ የወጣባቸው ንብረቶች አፈር በልቷቸው ሣር በቅሎባቸው እንዴትም የትም ተጥለው ይታያሉ፡፡

የምችለው እኔ የምመራው ቋሚ ኮሚቴን ነው። የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዋናነት የመንግስት በጀት እና ንብረት ህግ እና ሥርዓት በሚፈቅደው መንገድ ለታለመለት ዓላማ መዋል አለመዋሉን የማረጋገጥ ሥራን ይሠራል። የፋይናንስ እና የክዋኔ ኦዲት ላይ በስፋት ይሠራል። ከዚህ አንፃር እንደሚታወቀው ኦዲት ወደ ኋላ የሚሠራ ነው። የዘንድሮ የሚሠራው ከርሞ ነው። ከዚህ በፊት በነበረው የፓርላማ ዘመን የነበረው አስፈፃሚ ያከናወነው የ2012 እና የ2013 ዓ.ም የኦዲት ዓመት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ ይፋ መድረክ እናዘጋጃለን።

የኦዲት ባለድርሻ አካላት የሚባሉ የተለያዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አሉ። ፍትህ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ሥነምግባር እና ፀረሙስና ኮሚሽን፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር፣ ፕላንና ልማት ሚኒስቴርን የመሳሰሉት በተገኙበት ኦዲት ተደራጊዎች ይመጣሉ። ኦዲተር ጀነራሉ ቀርቦ ጥያቄዎችን አዘጋጅተን እንጠይቃለን። በትክክል መረጋገጥ የሚችሉ ማስረጃ ያላቸው ጉዳዮች ቀርበው ምላሽ ይሠጥባቸዋል። ነገር ግን የሚያስጠይቅ ነገር ሲያጋጥም ደግሞ ተጠያቂ ይደረጋሉ። ለአብነት ያህል ባለፈው ሳምንት ገንዘብ ሚኒስቴር 39 የሚደርሱ አስፈፃሚ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ወስዷል። ይህን ትዕዛዝ የሠጠው ቋሚ ኮሚቴው ነው። ቋሚ ኮሚቴው ሁልጊዜም ይፋዊ መድረኮችን ሲያዘጋጅ መጨረሻ ላይ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል። የኦዲት ማሻሻያዎች እንዲቀርቡለት ቀነ ገደብ ያስቀምጣል። የገንዘብ ሚኒስቴር አስተዳደራዊ እርምጃዎችን መውሰድ እንዲችል በአዋጅ የተፈቀደለት መብት ያለው በመሆኑ ማስጠንቀቂያን መፃፍ እና የገንዘብ ቅጣት ማስቀመጥ ይችላል። ስለዚህ 39 አካላት ላይ እንዲህ አይነት ውሳኔን አስተላልፏል።

የፍትህ ሚኒስቴር ደግሞ እነዚህ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተላለፈባቸው የወንጀል ጥያቄን የሚያስከትሉ ወይም የማያስከትሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ከሆኑ በቂ ምርመራ አድርጎ እነርሱን እንዲወስድ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል። አሁን የምርመራ መዝገቦችን እያደራጀባቸው ያሉ ባለሞያዎች እና የሥራ ሃላፊዎች ስለመኖራቸው መረጃዎች አሉን። ሲደርስ ለመገናኛ ብዙሃን በፍትህ ሚኒስቴር በኩልም ሆነ በእኛ በኩል ይፋ የሚደረጉ ይሆናሉ። ነገር ግን አሁንም በተጨባጭ ክስ የተመሠረተባቸው ባለሞያዎች አሉ። እንደምክር ቤት ግን የእኛ ዋነኛ ተልዕኮ አመራር እና ባለሞያዎችን መክሰስ ተቋማትን ማንኳሰስ አይደለም።

ዋነኛ ተልዕኳችን እና ፍላጎታችን እነዚህ አስፈፃሚ ተቋማት የኦዲት ግኝት ማሻሻያ አድርገው ቋሚ ኮሚቴው በሚያደርገው ድጋፍ ከነበሩበት የተበላሸ አሠራር እንዲላቀቁ ማስቻል ነው። በተሻለ ቅልጥፍና እና ፍጥነት ማገልገል የሚችል ተቋም እንዲገነባ ነው። ምክንያቱም አገር የምትመሰለው በተቋማት ነው። ጠንካራ ተቋም ያላት አገር ጠንካራ ትሆናለች። ዜጎች የተቀላጠፈ አገልግሎት ያገኛሉ። የእኛ ዋነኛ ፍላጎት ያ ነው። ግን ደግሞ ማንኛውም አመራርም ሆነ ባለሞያ የተጣለበትን የሕዝብ አደራ በአግባቡ የማይወጣ ከሆነ ሌብነትን ማስቆም እና መቅጣት ያስፈልጋል። ይህንን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በባዕለ ሲመታቸው በይፋ ለህዝብ የገቡት ቃል ኪዳን አለ። መንግስታቸው ሌብነትን በፅኑ እንደሚዋጋ ቃል ገብተዋል። እኛም ከዚህ ጋር ተያይዞ በምንሠራው የቁጥጥር ሥራ እንቅፋት አልገጠመንም። የምንሰጣቸው ትዕዛዞችም እስከ አሁን ተፈፃሚ እየሆኑ ነው። ይህ ግን በቂ አይደለም። የምር ቁርጠኝነት ያስፈልጋል።

አንዳንድ የኦዲት ግኝቶች በተለይ የክዋኔ ኦዲት ላይ ያሉት የንብረት ብልሽቶች አስደንጋጭ ናቸው። ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ የወጣባቸው ንብረቶች አፈር በልቷቸው ሣር በቅሎባቸው እንዴትም የትም ተጥለው ይታያሉ። ይሔ እንደ ኢትዮጵያ ባለች ድሃ አገር ተቀባይነት የለውም። በእርግጥ የኦዲት ግኝት ማለት ሁሉም የተበላ የተመዘበረ ነው ማለት አይቻልም። ምናልባት ያልተመዘገበ ሊሆን ይችላል። ይህ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል። ዋናው ነገር ግን ተጠያቂነትን ለማስፈን ቁርጠኛ የሆነ ምክር ቤት አለ። ነገር ግን ምክር ቤቱ ተጠያቂነትን ለማስፈን ቁርጠኛ ቢሆንም የኢትዮጵያ ተቋማት በሙሉ ከብልሹ አሠራር የፀዱ ይሆናሉ ማለት አይደለም። የፍትህ ተቋማት የፀጥታ አካላት ብርቱ ጥረት ማድረግ አለባቸው። መገናኛ ብዙሃን ተኪ የለሽ ሚናን መጫወት አለባቸው። መሠል ጉዳዮችን የምርመራ ጋዜጠኝነትን መሠረት አድርጎ ብልሹ አሠራርን በማጋለጥ ማህበረሰቡ ምክር ቤቱንም የሚደግፍ ሞጋች እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል።

በተባበረ ክንድ የኢትዮጵያ ተቋማት የሚታሰበውን በጎ ተስፋን የሚመጥኑ፤ ያለፈውን ብሶት ማካካስ የሚችሉ ተቋማዊ ቁመና ላይ እንዲገኙ የሚያስችል መደላድል ከተፈጠረ ቀጣዩ ምክር ቤት ደግሞ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመጨመር የተሻለ የህዝብ ተቀባይነት ያለው ይሆናል። ይህ እንዲሆን የተቻለንን ሁሉ እየሠራን ነው። ተጠያቂነትን ለማስፈን ዝግጁነት አለ ወደ ትግበራውም እየገባን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ ብልሹ አሠራርን በሚመለከት የተወሰነ ነገር ብለዋል። አሁን በሚካሔዱ የህዝብ መድረኮች ተደጋግሞ የሚነሳው ይኸው የብልሹ አሠራር እና የሌብነት ጉዳይ ነው። በእርግጥ 6ኛው ምክር ቤት አንድ አመት ብቻ አሳለፈ ብንልም አንድ አመትም ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀላል አይደለም። በእርግጥ ምክር ቤቱ ሌብነትን ለመከላከልም ሆነ ብልሹ አሠራርን ለመቀነስ ሚናውን እየተወጣ ነው?**

**አቶ ክርስቲያን፡-** አስቀድሜም ገልጬዋለሁ። በተሟላ መልኩ ሚናውን እየተወጣ ነው ለማለት ያዳግታል። አሁን እንደአገር ዋነኛ ትኩረታችን የአገርን ቀጣይነት ማረጋገጥ ላይ ነው። ምክር ቤትም፣ አስፈፃሚውም ሁሉም ኢትዮጵያን ለማፍረስ ፍላጎት ያላቸው ስብስቦች መኖራቸውን አውቆ እዛ ላይ እየሠራ ነው። ይሔ ለፕሮፓጋንዳ ሳይሆን በተግባር ያንን የጥፋት ዕቅዳቸውን ለመተግበር በመንቀሳቀስ በህዝባችንም ላይ ከፍተኛ በደልን ያደረሱ ማህበራዊ ቀውስ እየፈጠሩ ስለነበር ያንን ቀውስ መቀልበስ ላይ እንደነበርን አይካድም። ምክር ቤቱ ሙሉ ትኩረቱን በምክር ቤታዊ ሥራ ላይ ባላደረገበት ሁኔታ የሚጠበቅበትን ሃላፊነት በሙሉ ተወጥቷል ማለት አይቻልም።

ይህም ቢሆን ግን ትርጉም ያላቸው ሥራዎች ተሠርተዋል የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም በተጨባጭ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ወደ ተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በመንቀሳቀስ መሬት ላይ ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታም ሆነ የፍትህ እና የፀጥታ ሁኔታዎችን በሚመለከት ህብረተሰቡን በማነጋገር ጭምር ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወስዱ የምክር ቤት አባላቱ ሚናቸውን እየተወጡ ነው። ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲያስተባብሩላቸው በተመደቡላቸው አስፈፃሚ ተቋማት በመከታተል ማስተካከያ እንዲያደርጉ ሲሠራ ቆይቷል። የሚታቀደው ዕቅድ የህዝብን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ መሆኑን ክትትል በማድረግ ሲገመገም ነበር። መገምገም ብቻ አይደለም፤ በቀጣይ የመቶ ቀናት ዕቅዳቸው ውስጥ እንዲያካትቱ አቅጣጫ ሲያስቀምጥ ነበር። ይሔ በጎ ጅምር ነው። ነገር ግን ለዘመናት የተከማቸውን የሕዝብ ችግር ሊቀርፍ የሚችል አይደለም። እንኳን መቅረፍ ሊያስታግስ የሚችል አይደለም። እንቅልፍ አጥተን ሌት ተቀን መሥራት ይኖርብናል። ይሔ ከተለመደው ምክር ቤት ከፍ ያለ ምናልባትም የህዝብን ፍላጎት ከማሳካት፣ የአገር አንድነትን ከማስቀጠል የህዝብን ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር በአርበኝነት መንፈስ መሥራት ያለበት፤ ሁለንተናውን ለአገር አንድነት እና ለህዝብ ደህንነት መስጠት ያለበት ነው። ይህ የምክር ቤቱ እና የትውልዱ ሃላፊነት ነው የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ**

**አቶ ክርስቲያን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## “ኢትዮጵያ ታምርት ” ለአምራቾች አዲስ መንገድ

**አሥመረት ብሥራት**

በመዲናችን አዲስ አበባ “ኢትዮጵያ ታምርት” በሚል መሪ ቃል የአዲስ አበባ የስራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት አምራቾችን አቅም የማሳደጊያ የምክክርና ንቅናቄ መድረክ ተካሂዶ ነበር። መድረኩ የከተማችንን አምራች ኢንዱስትሪዎች አቅም ለማጎልበት ያቀደ ብሎም ያሉባቸውን ችግሮች አዳምጦ ለመፍታት ታስቦ የተዘጋጀ እንደነበር የዝግጅት ክፍላችን በቦታው ተገኝቶ ለመታዘብ ችሏል። በእለቱ የነበረውን ሁነትም ከዚህ እንደሚከተለው በመዳሰስ ለእናንተ አንባቢዎቻችን ይዘንላችሁ ቀርበናል።

በእለቱ ማልዶ በቦታው የተገኘው ታዳሚ ውጤታማ የተባሉትን መካካለኛ ኢንዱስትሪዎችን ጎብኝቷል። በአዲስ አበባ አራዳ ክፍለ ከተማ ሳንፎርድ ትምህርት ቤት አካባቢ የሚገኝ ደረጃውን የጠበቀ፤ ከውጭ የሚገባውን መተካት የሚችል ሶፋ የሚያመርት ኢንዱስትሪን ፤ በመቀጠል በርካታ የሰው ሀይል በውስጡ ይዞ የሚያሰራ አንድ ጋርመንት ተጎብኝቶ ወደ አዳራሽ ነበር የተገባው።

**ንቅናቄው ለምን አስፈለገ?**

በዋናው የውይይት መድረክ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባና የስራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊው አቶ ዣንጥራር አባይ፤ በከተማዋ ከተያዘው እቅድ አንዱ “ኢትዮጵያ ታምርት” የሚለው ንቅናቄ መሆኑን አንስተው በዚህም ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ከፍ ለማድረግ ይረዳል ብለዋል። በተጨማሪም ንቅናቄው አሁን ካሉት 10 ሺህ 504 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በጥራትና ቁጥር ወደ 26 ሺህ 260 ለማሳደግም እንደሚረዳ ነው ያነሱት። እነዚህ ኢንዱስትሪዎች አማካይ የማምረት አቅማቸውን ከ42 ነጥብ 6 በመቶ ወደ 85 በመቶ እንዲደርስ ታቅዶ ወደ ስራ መገባቱንም አመላክተዋል። ተኪ ምርቶችን በማምረት የውጭ ምንዛሪ ገቢን ማሳደግ አንዱ የስትራቴጂክ እቅድ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ዣንጥራር ተኪ ምርት አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሰፉ በማድረግ ከነበሩበት 418 ወደ 1 ሺህ 226 ለማሳደግ ታቅዷል። ወደ ውጭ የሚላከው የኢንዱስትሪ ምርት ከነበረበት 133 ወደ 381 በማድረስ፤ የውጭ ምንዛሪ ከነበረበት 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዶላር ወደ 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር የማስገኘት እቅድ መኖሩንም አብራርተዋል።

“ያለ ኢንዱስትሪ ልማት ያደገ አገር የለም” የሚሉት አቶ ዣንጥራር እንደ አገር ለመበልፀግ የተለያዩ ፖሊሲዎችን አሻሽሎ ከኢንዱስትሪያሊስቶች ጋር ተቀራርቦ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል። የሚሰሩ እጆችን ከስራ ጋር በማገናኘት ከተለመደው መንፏቀቅ ለመውጣት የተለየ ንቅናቄ ማስፈለጉንም አብራርተዋል። በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ኢንዱስትሪዎች መካከል 40 በመቶ የሚሆኑት በአዲስ አበባ የሚገኙ መሆኑን ጠቅሰው እነዚህ ኢንዱስትሪዎች ማምረት ከሚጠበቅባቸው አቅም 50 በመቶ ብቻ እያመረቱ እንደሆነ ተናግረዋል። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች የተጠቀሱ ሲሆን በቀጣይ 10 ዓመታት ውስጥ በየአመቱ መሻሻል እየተደረገ 85 በመቶ የምርት መጠን ላይ ለማድረስ እየተሰራ እንደሆነ ገልፀዋል።

ከሁለት ሺህ በላይ ኢንተርፕራይዞች ከቦታ፣ ከመብራት ከብድር እና ሌሎች ችግሮቻቸው እንዲፈታላቸው መደረጉን የተናገሩት አቶ ዣንጥራር ከ3 ሺህ በላይ ኢንዱስትሪዎች አሁንም የመብራት፣ የውሀ፣ የብድር፣ የውጭ ምንዛሬና ሊፈቱላቸው የሚገቡ በርካታ ተግዳሮች እንዳሉባቸው ያስረዳሉ። ቀደም ሲል የተቋቋሙ ለአመታትም ወደ ምንም ዘርፍ ሳይለወጡ ባሉበት ሲሰሩ የቆዩ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ተደርጎላቸው ከፍ ባለ ደረጃ እንዲለወጡ የሚሰራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ዣንጥራር መፈታት ያለባቸው ችግሮች ተፈተው በአገሪቱ ያሉ ኢንዱስትሪዎች ተኪ ምርት አምራች እንዲሆኑ ብሎም የውጭ ምንዛሪን የሚያስገኙ ለማድረግ በትኩረት የሚሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

**የከንቲባዋ መልእክት**

በመርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው “አብዛኛው የአገራችን ዜጎች አምራች እድሜ ላይ የሚገኙ በመሆኑ ተባብረን ስርተን በአጭር ጊዜ የብልፅግና ማማ ላይ እንደርሳለን” ብለዋል። የዜጎችን ኑሮ ማሻሻልና የከተሞችን የስራ እድል ፈጠራን ለማሳደግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች ተቀርፀው ወደ ስራ ተገብቷል ነው ያሉት።



በአዲስ አበባ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች በከተማ አስተዳደሩ የስራ ሀላፊዎች ተጎብኝተዋል፤



የከፍታ ማማ ላይ ወጥተው የምናያቸው አገራት መነሻቸው ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በሰጡት ትኩረት ነው የሚሉት ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፤ እድገት ያለ ጥረትና ድካም ከቶውንም አይታሰብም፤ ራዕይን ማጥራት፣ ለሥራ ያለንን ፍቅርና ትጋት ማሳደግ፣ ጊዜያችንንና ሀብታችንን በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ ይገልፃሉ። በከተሞች ለስራ ፈላጊዎች የተለያዩ አማራጮችን ለማመቻቸት የስራ እድል ማጠናከርና የተቀናጀ የኢንዱስትሪ ድጋፍን ማከናወን ዋና አጀንዳ ሊሆን እንደሚገባም ያነሳሉ። የስራ መዳረሻ አላማው የስራ ክቡርነትን ባህል በማድረግ፤ የማምረትና አገር ውስጥ ፍጆታን ከመሸፈን ባሻገር በዓለም ገበያ ውስጥ በብቃት መግባትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል ብለዋል።

“በስራ ለውጥን ለማግኘት የሚተጉትን ለማግኘት፤ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይገባል” የሚል መልእክት ያስተላለፉት ከንቲባዋ፤ ስራን የመናቅ አስተሳሰብን ከውስጥ በማውጣት ለለውጥ መትጋት እንደሚገባ አሳስበዋል።

**የአምራች ኢንዱስትሪ ፈተናዎች**

በንቅናቄው ተሳታፊ በነበሩ አምራቾች በመድረኩ የተለያዩ ሀሳቦች ቢነሱም በዋነኛነት የፋይናንስ እጥረት ስራቸውን አስፋፍተው እንዳይሰሩ እንዳደረጋቸው፤ ለብድሮች መያዣ ተብለው የሚጠየቁት ንብረት ከአቅም በላይ የሆነ የተለያዩ የቢሮክራሲ መስመሮች ስራውን በተቃና መልክ እንዳይሄድ ፈተና እንደሆነባቸው ተናግረዋል። የባልትና ውጤቶችን ለውጭ ገበያ እያቀረብን ገበሬዎች እና ነጋዴዎች ሚዛን እንዲያነሳላቸው የደረቀው በርበሬ ዛላ ላይ ውሀ ያርከፈክፉበታል። ይሄም ሻጋታ ‹‹አፍላ ቶክሲን›› ያጋልጣል። በመሆኑም ስለአፍላ ቶክሲን በቂ ግንዛቤ ስለማይኖራቸው ይህን ለመከላከል ከቻይና በርበሬ እያስመጣን እስከመጠቀም ደርሰናል ነው ያሉት። ጥራት ያለው ግብአት አቅራቢ ቢመቻችልን የሚል ጥያቄም ተነስቶ ነበር። የሀይል አቅርቦት ችግር፤ ሰፊ የማምረቻ ቦታ ማጣት፤ ስልጠናዎችን የሚፈልጉ አምራቾች የክህሎት ስልጠና አለማግኘታቸው፤ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና ሌሎችም ጉዳዮች የተነሱ ሲሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል።

**የባለድርሻ አካላት ሚና**

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አቶ መላኩ አለበል በሰጡት ምላሽ እንዳሉት፤ እንደ አገር የውጭ ምንዛሪ የሚያስቀሩ ተኪ ምርት አምራቾች በብዛት ስለሚያስፈልጉ ችግሮችን በመቅረፍ ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ ጥረት ይደረጋል ብለዋል። አምራቾች ከአስፈፃሚ አካላት ጋር በቅርበት መገናኘታቸው ችግሩን በጥልቀት ታይቶ እንዲፈታ ለማድረግ ትልቅ መንገድ እንደሚከፍት ተናግረው፤ እያንዳንዱ ችግሮ በሙያተኞች እየተለዩ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥባቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

“አምራች ኢንዱስትሪዎች በሀይል አቅርቦት ምክንያት ስራቸው እንዳይስተጓጎል እየሰራን ነው” ያሉት በእለቱ የተገኙት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተወካይ በበኩላቸው የሀይል አቅርቦት ጥያቄ ለሚያቀርቡ ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ የሚሰጥበት አግባብ መኖሩን አስረድተዋል። ከዚህ ቀደም ለነበሩት ክፍተቶች በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ሰብስቴሽኖች አቅም መሙላት እንዲሁም ኢንዱስትሪዎቹ የሚያቀርቡት የኃይል ፍላጎትና አጠቃቀም አለመመጣጠን፣ የተሰጣቸውን የኃይል መጠን በአግባቡ አለመጠቀም እና የነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች አመሰራረት በኢንዱስትሪ ዞን የተጠቃለለ አለመሆን በኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ግንባታ እና ማሻሻያ ላይ ተግዳሮት መሆኑንም አመላክተዋል።

ከልማት ባንክ የመጡት ተወካይ በበኩላቸው በሰጡት ምላሽ፤ ለማሽን ማስገቢያ ተብሎ የተዘጋጁ ብድሮች ከግንዛቤ እጥረት ይሁን ከሌላ ብዙም ተጠቃሚ እንደሌላቸው ጠቅሰዋል። አምራቾች በርቀት ይህ ገጥሞናል ከማለት ባሻገር በቅርበት በመገናኘት የገንዘብ ማግኛ አመራጮችን መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል። የውጭ ምንዛሪ እጥረትም እንደ አገር የተከሰተ ሲሆን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ቅድሚያ በመስጠት አስፈላጊው ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን አስረድተዋል። በማይክሮ ፋይናንስ በኩል የሚጠየቁ መያዣዎች አስፈላጊነት የሚታይ መሆኑን ጠቅሰው ሌሎች የቢሮክራሲ ጉዳዮችን የማጥራት ስራ የሚሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

**የመፍትሄ ሃሳቦች**

ማጠቃለያውን የሰጡት አቶ ጃንጥራር የአቅርቦት ችግር ኖሮብን ከቻይና በርበሬ እያስመጣን ነው ለተባለው ሀሳብ በቀጥታ ከገበሬዎች ህብረት ስራ ጋር በመገናኘት ጥራት ያለው ምርት እንዲያገኙ የሚደረግ የአሰራር ስርዓት የሚዘረጋ መሆኑን ጠቅሰዋል። በተለይ በአገር ውስጥ ግብአት መሸፈን የሚችሉ ኢንዱስትሪዎች የውጭ ምንዛሪ መባከናቸው አግባብነት እንደሌለው አብራርተዋል። የቦታ ጥያቄ የሁሉም ኢንዱስትሪዎች ጥያቄ መሆኑን በማስረዳትም አንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ቦታን እንደ ሀብት መያዝ የመፈለግ አዝማሚያ እንዳላቸው ገልፀዋል። ይህ አካሄድ ግን ትክክለኛ ያልሆነ አካሄድ መሆኑን ተናግረዋል። ቦታን እንደማምረቻ፤ እንደሀብት ማግኛ አድርጎ ማሰብ ውጤታማነት ላይ እንዲያተኩሩ የሚረዳቸው መሆኑን ጠቅሰው ከተማዋ ካለባት የቦታ እጥረት አንፃር በአንድ አካባቢ በሚገነቡ ማምረቻዎች ይሄንን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ስራ የሚሰራ መሆኑን አብራርተዋል።

“የተነሱ ችግሮች በሙሉ ባለቤት ያላቸው በመሆናቸው በቀላሉ ተፈተው ወደ ምርታማነት እንደምንሸጋገር ተስፋ አለኝ” ያሉት አቶ ጃንጥራር፤ ስልጠናዎች የአቅም ማጎልበቻ መድረኮች በየጊዜው እየተዘጋጁ አምራቾችን ወደ ውጤት የማምጣት ስራ ትኩረት የሚያገኝ ትልቅ ጉዳይ መሆኑን ያስረዳሉ። ኢንዱስትሪዎች ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ፤ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ፤ ብሎም ወደ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገሩ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካል ስራውን አውቆ መስራት እንደሚገባው አሳስበዋል። አምራቾችም እንቅፋትን ሳይፈሩ ወደ ፊት የሚያሻግራቸውን መንገድ በሙሉ መሞከር እንደሚገባቸው አብራርተዋል።

**እንደ መውጫ**

በመርሀ ግብሩ ማጠናቀቂያ ላይ ለኢንዱስትሪዎች የምስጋናና የእውቅና አሰጣጥ ስነ ስርአት ተካሂዷል። በእለቱም ለሁለት ጥቃቅንና ለሶስት አነስተኛ ኢነተርፕራይዞች፤ ለስድስት መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፤ ለአምስት ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የእውቅና ሰርተፍኬትና ዋንጫ በእለቱ የክብር እንግዶች ተበርክቷል።

አገር እንድታድግ፤ ያለአግባብ የሚወጣ የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በሚመረት ተኪ ምርት መቀየር አስፈላጊ መሆኑ ሊታመንበት ይገባል። ብሎም ወደ ውጭ አገር በመላክ የውጭ ምንዛሪ አቅማችንን ከፍ ለማድረግ አምራቾች ሊበረታቱ ይገባል። ዓለም በተለያየ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በምትናጥበት የውስጥ አቅምን በአገር ልጆች እውቀት ከመገንባት የሚበልጥም አማራጭ የለምና ይህ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። በቀጣይም በርካታ ስራ አጥ ወጣቶችን የሚሰበስቡ ኢንዱስትሪዎች በማበራከት የኢትዮጵያን እድገት በአስተማማኝ መሰረት ላይ ማፅናት ይጠበቅብናል በሚለው የመርሀ ግብሩን ማጠቃለያ ሀሳብ አበቃን።

# ጎሜ

# የጠጅ ፖለቲካ .... ከብሄር እስከ ሃይማኖት

**ሙሉቀን ታደገ**

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ሁለንተናዊ በሆኑ ክርክሮች መሐመድ ይመርን ከረታ ወዲህ ከጧት የጀመረ እስከ ማታ ድረስ መጮሁን አቁሞ ነበር። ከሰሞኑ ግን የእድር እና የሰፈራችን ሁኔታ አልጥምህ ቢለው በፊት ያደርግ እንደነበረው ጠዋት ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል ጀምሮ ጨለማው ለአይን ያዝ እስከሚያደርግ ድረስ ይጮህ ይዟል። ለዚህ ደግሞ ሁለት ምክንያቶች እንዳሉት የቅርብ ሰዎች ይናገራሉ ። የእድር መሪዎቻችን እና እድራችንን ለመምራት የሚፎካከሩ ሃይሎች የእድራችንን ህልውና በጠጅ ፖለቲካ እየተፈታተኑት መሆኑ አንደኛው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በየጊዜው የእድር መሪዎቻችን እና ተፎካካሪዎቹ በሚፈጥሯቸው አላስፈላጊ አጀንዳዎች እየተታለሉ የሰፈራችን እና የእድራችን ህልውና አደጋ ላይ ለመጣል የሚራኮቱ ዜጎች በሚወስዱት ግብዝነት የተሞላበት እርምጃ እረፍት በማጣቱ ነው ።

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ዋርካው ስር በሚገኘው ድንጋይ ላይ ቆሞ መጮህ ሲጀምር ሁሉም የሰፈራችን ሰዎች ሴት ወንድ፤ ህጻን አዋቂ ሳይሉ በመሰባሰብ የወፈፌውን ሚስጥር አዘል ንግግር ማዳመጥ በሰፈራችን እየተለመደ የመጣ ባህል ነው። ይልቃል አዲሴ ዛሬም ከእድራችን መሰብሰቢያ ዋርካ ስር በሚገኘው ድንጋይ ላይ ቆሞ መጮህ ሲጀምር የሰፈራችን ሰዎች ተገልብጠው ወደ ዋርካው በመሄድ በጩኸቱ ውስጥ የሚሰሙትን ቅኔ አዘል ሚስጢሮች ሊኮሞኩሙ ተሰባስበዋል።

ይህ በእንዲህ እያለ ከተሰብሳቢዎች መካከል አንዱና በሰፈራችን አብሿም እየተባለ የሚሰደበው ዘረ- ሰናይ ጉግሳ ማንም እንዲናገር እድል ሳይሰጠው ከተቀመጠበት ተነስቶ ለመሆኑ የጠጅ ፖለቲካ ምንድን ነው ? ሲል ንግግር ሲያደርግ የነበረውን ይልቃል አዲሴን አቋረጠው።

አብሿሙ ዘረ- ሰናይ ጉግሳ ንግግሩን በማቋረጡ ምንም ሳይከፋ ... ይልቃል አዲሴ የጠጅ ፖለቲካ ምን እንደሆነ ለማብራራት ጉሮሮውን ጠራርጎ ንግግሩን ጀመረ። ከዚህ በፊት በአንድ ጹሁፍ ላይ ገልጨው ነበር። ዛሬም ማስታወሱ አይከፋም ። እየውላችሁ የጠጅ ፖለቲካ ማለት ግልጽ እንዲሆንላችሁ አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ።

በአንድ ወቅት በሰፈራችን የሚኖር ከባህላዊ መሳሪያዎች እስከ ዘመናዊ ፋብሪካዎች የሚያመርቱትን የመጠጥ አይነቶችን ምንም ሳያማርጥ የሚጠጣ ሰው ነበር። ምን አለፋችሁ የአልኮል በርሜል በሉት....!

ይህ ሰው በስራ ምክንያት መጠጥ በሌለበት አካባቢ ይመደባል። በዚህም መጠጥ ባለፈበት ሳይሄድ ለሳምንታት ይሰነብታል። በመጨረሻም ስራውን ጨርሶ ወደ ሰፈሩ ተመለሰ። ወደ ሰፈሩ እንደተመለሰም ወደ ቤቱ ገብቼ ቤሰቦቼን እንኳን እንዴት እንደሰነበቱ ልጠይቅ ሳይል የመስክ ቦርሳውን ከሰፈራቸው መንገድ ዳር በምትገኝ ሁለገብ የሸቀጥ መሸጫ ሱቅ ላይ ወርውሮ እየተቻኮለ ወደ ጠላ ቤት አመራ ። አንድ ሁለትም አለ። ይሁን እንጂ በስራ ምክንያት ለሳምንታት ተለይቶት የነበረውን የመጠጥ ሱሱን ማርካት ባለመቻሉ ወደ ጠጅ ቤት መሄድ ፈለገ። ከጠላ ቤቱም ወጣና ወዲያውኑ ጠጅ ቤት ገባ። ይህንን ጠጅ ይኮመኩም ያዘ። ይሁን እንጂ አሁንም የመጠጥ ሱሱን ማርካት አልቻለም። የመጠጥ አምሮቱ ባለመውጣቱ አረቄ መጠጣት አስቦ ከጠጅ ቤት ወጥቶ ወደ አረቄ ቤት ጎራ አለ። ኮማሪዋን አረቄ አዘዘ። ኮማሪዋም የታዘዘችውን አረቄ ቀድታ ጠረጴዛ ላይ አኖረች። አቶ የመጠጥ በርሜልም ከመቅጽበት አረቄውን ከጠረጴዛው አንስቶ ፉት አለ። የመጠጥ ልክፍቱን ያልተወጣው ሰው ከአረቄው በፊት ጠጅ ጠጥቶ ስለነበር ገና ከአረቄው አንድ ጊዜ እ..ፉት... እንዳለ ሊያስመልሰው አነቀው።

ለዚህም ዋናው ምክንያት ጠጅ በባህሪው መጀመሪያ ወደ ሰዎች ሆድ ከገባ በኋላ ሌላ መጠጥ እንጨርብህ ቢባል ቆይቶ የመጣውን መጠጥ ለማስገባት አለመፈለጉ ነው። ምን አልባት መጠጥ የሚጠጣው ሰው ሌላ መጠጥ መጠጣት ፈልጎ ቢቀመስ ወዲያውኑ ሊያስመልሰው ይችላል። እኔ ባለሁበት ሆድ ውስጥ ከእኔ ውጭ ሌላ ምንም አይነት መጠጥ አላስገባም ማለቱ የጠጅ ሁነኛ የስግብግነት መለያው ነው።

> **"ከሰሞኑ በሃይማኖት ስም የተደረገው እያንዳንዱ ድርጊት ሰፈራችንን እና እድራችንን ለማተራመስ የተደረገ የፖለቲካ ግብግብ ነው"**

ለማንኛውም ወደ ተነሳሁበት ወግ ልመለስና ከመጠጥ እርቆ የሰነበተው ሰው በጠጅ ላይ አረቄ ሊጨምር ቢል ስግብግቡ ጠጅ አረቄን አላስገባም አለ። በዚህ ጊዜ የሰውየውን መጠጥ አለመጥገብ ያየችው አረቄ ጠጅን ምን ብትል ጥሩ ነው....... ካስገባህ አስገባኝ ሰውየው እንደሆነ ገና አልጠገበም አረቄም መጨመር ይፈልጋል። ሰውየው እኔን ሲጠጣ አላስገባም ካልከኝ ግን ሰውየው ያስታውክና ሁለታችንም ከውጭ ወድቀን እናድራለን ። የማንም ሰካራም ሲረግጠን ነው የምናድረው። ስለዚህ በሰላም አስገባኝ አለችው አሉ።

ይሄን ወደ እኛ ሰፈር የእድር አስተዳደር ዘይቤ ስናመጣው ከእራሳችን ጎሳ ውጭ በሰፋራችን እና በእድራችን ማንንም ሰው እንዲኖር አንፈቅድም የሚል አንድምታ አለው። በጎሳ ፖለቲካ ሲታወክ የሰነበተው እድራችን ከሰሞኑ ደግሞ በሃይማኖት ምች ሲታመስ የእየተስተዋለ ነው። እውነት ለማናገር የማንከባበር እና አንዱ አንዱን በፈለገው ቦታ እንዲቀመጥ የምንከለክል ከሆነ አረቄ እንዳለችው ሁላችንም ውጭ ወድቀን እናድራለን። የማንም ሰካራም መጫዎቻ መሆናችን የማይቀር ነው።

አንዴ ንግግር ከጀመረ መናገር የማያቆመው ይልቃል አዲሴ ንግሩን ቀጥሎ...ከሰሞኑ በሰፈራችን እና በእድራችን የተመለከትነው የጠጅ ፖለቲካ ከወለዳቸው መፈክሮች ደግሞ የሚያስገርሙ መሆናቸው ያስረዳል። ሁሉንም መጥቀስ ባይቻልም አለ ይልቃል አዲሴ፤ አንድ ሁለቱን ላስታውሳችሁ ብሎ ያልበላውን ጢሙን በማከክ ንግግሩን ገታ አደረጋና ከአፍታ ቆይታ በኋላ ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ .....

ከሰሞኑ ከተመለከትኳቸው መፈክሮች ውስጥ የፈጣሪአቸውን ስም እየጠሩ ከእነሱ ሃይማኖት ውጪ ያሉ ሰዎችን እናጠፋልን የሚለው አንዱ ነው። የትኛው እምነት ነው የፈጣሪን ስም እየጠራችሁ ሰዎችን ግደሉ ፤ ቤተ እምነቶችን አቃጥሉ የሚለው? ጉድ እኮነው ! አይ የጠጅ ፖለቲካ ... ሲያሳብድ እኮ ቅጥ የለውም።

ሌላው ከሰሞኑ ሃይማኖትን ሽፋን ተደርጎ ከታዩ አስገራሚ መፈክሮች መካከል የአጼዎችን አገዛዝ ለማምጣት የምትናፍቁ ሃይሎች የአጤዎች ስርዓት ላይመለስ ተቀብሯል። የተቀበረን ስርዓት ለማምጣት የምትደክሙ ሰዎች በከንቱ አትልፉ የሚል ነው። የአጤው ስርዓት እንዲመለስ ከማይፈልጉ ሰዎች መካከል አንዱ እኔ ብሆንም የአጤዎቹ ስርዓት በእስልምና እና በክርስትና ሃይማኖቶች ላይ የሰሩት በደል ግን ፈጽሞ አይታየኝም።

ስለ እውነት ከሰሞኑ በሰፈራችን ለተፈጠረው ስርዓት አልበኝነት ዋና መነሻ ሃይማኖት ከሆነ ስለምን የአጤዎችን ስም በክፉ ለመጥራት ፈለግን ? ክርስትና እና እስልምና ሁለቱም የመጡት በአጤዎቹ ዘመን በአጤዎቹ ይሁንታ አይደለም እንዴ?

የክርስትና እምነት በውጪ አለም መሰበክ በተጀመረ ጊዜ በርካታ የውጪ አለም ሰዎች ክርስትና ሃይማኖትን ተቀበሉ። በዚህም በንጉሳቸው ቀጭን ትዕዛዝ ክርስትናን የተቀበሉ ሰዎች እንደወንጀለኛ ተቆጥረው ለአስፈሪ አውሬዎች ተሰጡ። በሚነድ እሳት ውስጥም ተጨመሩ። በሰው ልጆች ይፈፀማል ተብሎ የማይታሰብ በደልም ተፈጸመባቸው። የእኛ ሰፈር ንጉስ ግን የክርስትና እምነት ሰባኪዎች ወደ እኛ ሰፈር በመጡ በቤተ መንግስቱ በማስቀመጥ ከመንከባከቡም ባለፈ ራሱ ንጉሱ የክርስትናን ሃይማኖትን ተቀብሎ እንዲስፋፋ በከፍተኛ ደረጃ ሰራ።

የእስልምና እምነት ተከታዮችም በተመሳሳይ በሳውዲ አረቢያ የእስልምና እምነት በተሰበከ ጊዜ የእስልምና እምነትን በመቀበላቸው እንደ ወንጀለኛ ተቆጥረው በቋራይሾች ተሳደዱ። የእስልምና አማኞችም ከቋራይሾ ግድያ በመሸሽ ወደ እኛ ሰፈር ንጉስ መጥተው ተደበቁ። በዚያን ጊዜስ የራሳቸው ሰዎች ቋራይሾች ያላዘኑላቸውን የእስልምና እምነት ተከታዮች ከሞት የታደጋቸው የእኛው ሰፈር ገዥ አጼው አይደለም እንዴ? የእኛን ሰፈር የተለያዩ እምነቶች መሰባሳቢያ ሙዚየም እንድትሆን የአደረጉ አጼዎች አይደሉም እንዴ?

ከሰሞኑ በሃይማኖት ስም የተደረገው እያንዳንዱ ድርጊት ሰፈራችንን እና እድራችንን ለማተራመስ የተደረገ የፖለቲካ ግብግብ እንጂ ሃይማኖት እንዳልነበር አንድ ማሳያ ልጥቀስ... በመካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ በዘይላ ወደብ የሚደረገውን እጅግ አትራፊ የሆነውን የንግድ ልውውጥ በበላይነት ለማስተዳደር በማሰብ በወቅቱ በሰፋራችን የነበሩ የክርስቲያን እና የእስልምና መሪዎች ወደ ከፋ ጦርነት ውስጥ ገቡ። የጸባቸው መነሻ ኢኮኖሚያዊ ሆኖ ሳለ የሁለቱም ሃይማኖት መሪዎች ጦርነቱንም ለማሸነፍ ሲሉ ሃይማኖታዊ ሽፋን ሰጡት። በዚህም የሰፈራችንን ሰዎች ለበርካታ ዓመታት በችግር እና በጦርነት አመሱት።

ከሰሞኑም የሰፈራችን ፖለቲከኞች እና የሰፈራችን ታሪካዊ ጠላቶች የፖለቲካ ጥማቸውን ለመወጣት ሲሉ ለእኩይ ፍላጎታቸው የግል ጥቅማቸውን የሃይማኖታዊ እሳቤዎችን በማላበስ ሰፈራችን ሲበጠብጡ ይስተዋላል። በዚህም በርካታ ሰዎችን ከግራ እና ከቀኝ ማሰልፍ ችለዋል። ይህ ደግሞ ለሰፈራችን ህልውና አደገኛ ነው።

ስለሆነም ከቀደመው በሃይማኖት ሽፋን የሰፈራችን ሰዎች የደረሰባቸውን መከራ ከራሳችን በደንብ አድርጎ በመገንዘብ የእድር መሪዎቻችን እና የሰፈራችን ታሪካዊ ጠላቶቻችን የፈጸሙብንን በደል ተገንዝባችሁ ከተጠመደላችሁ የመጥፋት ወጥመድ መውጣት ያስፈልጋል።

እነ ምስር እና ወዳጆቿ ሰፋራችንን እና እድራችንን ለማፍረስ መጀመሪያ በጦርነት ሞከሩ። በጦርነቱም መነሳት እንዳይችሉ አድርገን ክፉኛ አደባየናቸው። በጦርነት አልቻለን ሲሉ በብሄር ፖለከቲካ ሞከሩን። በዚህም ጉንፋን ሰፈራችንን ክፉኛ መረዙት። ግን እንዳሰቡት ሰፋራችንን ሊያጠፉት አልቻሉም ። የብሄር ጉንፋንን መቋቋም ስንጀምር ደግሞ በሰፋራችን የሚገኙ የነዋይ ሴሰኞችን ተጠቅመው በሃይማኖት ስም መጡብን ። ግማሾቻችን ሳናውቅ፤ ግማሾቻችን ደግሞ በግብዝነት ባጠመዱልን ወጥመድ ገባን።

ብሔርንም ሆነ እምነትን አስታከው ሰፈራችንን ለማወክ እና ለማበጣበጥ የሚመጡ ሃይሎችን እኩይ ሴራ የሚያከሽፍ ሃይል ከሰፈራችን ብቅ ማለት ሲጀምር የዝንጀሮ ፖለቲካ ተግባራዊ ያደርጉበታል። ብሎ ንግግሩን ሳይጨረስ አብሿሙ ዘረ- ሰናይ ጉግሳ የዝንጀሮ ፖለቲካ ደግሞ ምንድን ነው ? ሲል በድጋሚ ይልቃል አዲሴን ንግግር አቋረጠው።

ይልቃል አዲሴ አሁንም በአብሿሙ ዘረ- ሰናይ ጉግሳ ሳይናደድ የዝንጀሮ ፖለቲካን ትርጉም ያብራራ ያዘ። በአለም የፖለቲካ ፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የዝንጀሮ ፖለቲካ የሚል የፖለቲካ ፍልስፍና እንደሌለ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ በእኛ ሰፈር የነበረውንና ያለውን ፖለቲካ አካሄድ የዝንጀሮ ፖለቲካ ብየዋለሁ። ለምን የዝንጀሮ ፖለቲካ ተባለ ? የሚል ካለ ምክንያቱን እነሆ፡-

በአንድ የዝንጀሮ መንጋ ውስጥ አንዲት እናት ዝንጀሮ ወንድ ልጅ ከወለደች በልጇ እና በእሷ የሚደርስባቸው ግፍ ከኮሶ እጅጉን የመረረ ነው። ምክንያቱም የተወለደው ዝንጀሮ ወንድ ከሆነ የወደፊት መንጋው መሪ ሊሆን ይችላል በሚል ፍራቻ እና ስጋት በመንጋው የሚገኙ ትላልቅ ወንድ ዝንጀሮዎች በአዕምሯቸው ክፋትን ስለሚያረግዙ ነው። በዚህም ምንም የማያቀውን ህጻን ዝንጀሮ ለመግደል ይነሳሳሉ።

ይህን ተከትሎ እናት ዝንጀሮ ልጇን ለማትረፍ ከመንጋዋ ለመነጠል ትገደዳለች። ከመንጋቸው በተነጠሉበት ወቅት ምናልባትም ልጅና እናትን እስከ ሞት ሊዳያደርስ ለሚችል ለአስከፊ ችግር ሊጋለጡ ይችላሉ። ገና ለገና የወደፊት የመንጋው መሪ ይሆናል በማለት የራሱን የመንጋ አባል ማሰቃየት እና መግደል የዝንጀሮ ሁነኛ መታወቂያ ባህሪው ነው።

አሁንም በእኛ ሰፈር ያለው ገና ለገና የጠጅ ፖለቲካችንን ሊያከሽፍ ይችላል ተብሎ የሚገመት ሰው ከሰፈራችን ብቅ ማለት ከጀመረ የሰፈራችን የእድር መሪዎች እና የእኛ ሰፈር ታሪካዊ ጠላቶች ያንን ሰው ያለምንም ሃጢያቱ በመወንጀል ሊያጠፉት ይነሳሳሉ። ይህ ባህል አሁን ላይ በእኛ ሰፈር እንደ ትልቅ የፖለቲካ ብልሃት ተደርጎ እየተወሰደም ነው ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ በዋርካው ስር የተሰበሰቡ ሰዎች ንግግሩን በድጋፍ በጭብጨባ አቋረጡት። ከጭብጨባው በኋላ ያለውን የይልቃል አዲሴ ንግግር ለሚቀጥለው ሳምንት እናቀርባለን። እስከዚያው ከጠጅ ፖለቲካ እንዲጠብቃችሁ ምኞቴ ነው!!! ሰላም።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## አርበኝነት ባህል አርበኝነት ጥበብ

**ዋለልኝ አየለ**

ጀግንነት በኢትዮጵያ ውስጥ ልዩ ቦታ አለው። ለዚህም በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ባህሎችን ማስታወሱ በቂ ምስክር ናቸው። ከጥንታዊው የአደን ሕይወት ጀምሮ ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ጀግንነት ከባህል ጋር የተሳሰረ ነው። ከዘመን ዘመን የተለያየ ቢሆንም ዛሬም ድረስ ጀግንነት ትልቅ ዋጋ አለው። ለምሳሌ በቀድሞው ጊዜ «አንበሳ ገዳይ፣ ነብር ገዳይ» እየተባለ ይሞገስ ነበር። አነጣጥሮ ዒላማውን የሚመታ ሰው «ተኳሽ» እየተባለ ይጠራ ነበር።

እንደየዘመኑ የተለያየ መሆኑን የምናውቀው ደግሞ አሁን ላይ በምናየው የጀግንነት ትርጉም ነው። ጀግንነት እንደ ዘመኑ ሁኔታ ትርጉሙ እየሰፋ መጥቷል። ጀግንነት ከጦር ሜዳ ውሎ ወደ የልማትና መሰል ጉዳዮች መግለጫም እየሆነ ነው። ለምሳሌ በገጠር አካባቢ አንድ አርሶ አደር ለእርሻ አስቸጋሪ የሆነን ማሳ አሳምሮ አለሳልሶ ከታየ «እገሌ እኮ ጀግና ነው» ይባላል። በዝናብ ሲያርስ ፣ ሲያርም የታየ ገበሬ «አይ ጀግና» እየተባለ ሲሞገስ ይሰማል። ወደ ትምህርት ቤትም ስንሄድ አንደኛ የሚወጣ ተማሪ «የእገሌ ልጅ ጀግና እኮ ነው» ይባላል፤ በጓደኞቹ ዘንድም ትልቅ ክብር ይሰጠዋል።

ሌላው ጀግንነት በኢትዮጵያ ውስጥ ባህል መሆኑን የምናውቀው በሰርግ እና በሌሎች የድግስ ጉዳዮች ላይ ሲጫወቱ የሚወዳደሱት ጀግንነትን መሰረት በማድረግ መሆኑም ላይ ነው። በእዚህም የቀደምት አባቶችን ገድል መዘከር ብቻ ሳይሆን የአሁን ልጅም ጀግና መሆን እንዳለበት ይጠቁማሉ። አባቴ ጀግና ነበር ማለት ብቻ ሳይሆን ራሱ ጀግና ሆኖ ማሳየት እንዳለበት ለመጠቆም እንዲህ እየተባለም ይዘፈናል።

አርገው ሞቅ ሞቅ እንደ ደሬ ፍም
የአባት ጀግንነት ለልጅ አያልፍም!

ደሬ የሚባለው የዛፍ አይነት ነው፤ ሲደርቅ ማገዶ ይሆናል። የደሬ እንጨት ፍሙ ቶሎ አይጠፋም። ለዚህም ነው ደሬ የተባለውን እንጨት የመረጡት። የአባቱ ጀግንነት ብቻውን እንደማይበቃና ልጁም ጀግና መሆን እንዳለበት ለማስገንዘብ የሚቋጠሩ ስንኞች ናቸው።

የእረኞችን ጨዋታ እንኳን ብናስተውል በማሸነፍና በመሸነፍ ላይ የተመሰረተ ነው። ድንጋይ በማቆም ዒላማ መጫወትን ለእዚህ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ከርቀት ሆኖ የቆመውን ድንጋይ በተወርዋሪ ድንጋይ መምታት መቻል የጀግንነት ምልክት ነው። እረኞች ከኮባ ወይም ከሸንበቆ የተዘጋጀ ጠመንጃ መሰል ነገር መያዝ ይወዳሉ። ይሄ እንግዲህ ከማህበረሰቡ ተነስተው በአቅማቸው ልክ የትጥቅን አስፈላጊነት የሚገልጹበት ነው፤ ከስር ከስር እያሉ የሚያድጉበት።

ጀግንነት ጥበብ ነው። በጦርነት ታሪክ ውስጥ በተለይም ኢትዮጵያውያን በጥበብ እንደሚያሸንፉ በብዙ የታሪክ ጸሐፍት ተጽፏል። ታላቁን የዓድዋ ድል እንኳ ብንወስድ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀው የጣሊያን ሰራዊት በጦር፣ በጎራዴና በኋላቀር መሳሪያ ነው ውርደትን የተከናነበው። ለዚህም ኢትዮጵያውያን አርበኞች የተጠቀሙት ጥበብ ነው።

ዛሬ በምናከብረው የአርበኞች የድል ቀን እንኳ ብዙ ጥበብ የተሞላባቸው አሸናፊነቶችን መጥቀስ እንችላለን። «የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983» በሚለው በታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ መጽሐፍ ላይ እንደሰፈረው ራስ አበበ አረጋይ ይህን ስልት ተጠቅመዋል።

በ1932 ዓ.ም ራስ አበበ አረጋይ ለጣሊያን «እጀን ሰጥቻለሁ» በማለት ጣልያንን አጃጅለውት ነበር። ይህ መጭበርበር የደረሰበትም ምክትል እንደራሴና የሸዋ ገዥ የነበረው ጄኔራል ናዚ ነው። ራስ አበበ አረጋይ ለናዚ «እጄን ሰጥቻለሁ» በማለት ለአርበኞች ጓደኞቻቸው «አይዟችሁ እንዲህ እያልኩ እያታለልኳቸው ነው» እያሉ ይልኩባቸው ነበር። ናዚም ምንም ሳይጠረጥር እውነት መስሎት የሰላም ድርድሩን ተያያዘው። በኋላም ራስ አበበ አረጋይ ጦሩ ቀደም ሲል ከደረሰበት ጥቃት ማገገሙን ሲያረጋግጡ ጣሊያንን «ዞር በል!» በማለት ትግላቸውን ቀጠሉ።

ሌላኛው የጦርነት ስልታቸው ደግሞ በወቅቱ የማይጠረጠሩትን ሴቶችን ማሰለፍ ነበር። ለዚህም እነ ሸዋረገድ ገድሌና አርበኛ ከበደች ሥዩም ተጠቃሽ ናቸው። እዚህ ላይ በዓድዋው ጦርነትም የእቴጌ ጣይቱ ጥበብ ተዳጋግሞ መጠቀሱን ልብ ይሏል። የጣሊያን ምርኮኛ መስለው የሰራዊቱን ጥንካሬና ድክመት ያጠኑ ሰላዮችም ነበሩ።

> ጣሊያን ኮሶ ጭኖ ሸዋን ሲያጠጣው
> ገና ሲበጠብጥ ዳኘውን ቀናው
> ቅዳሜ ተግዞ እሁድ ተበራየ
> መስኮብም ገረመው ጣሊያንም ጉድ አየ!
> አገርክን ምኒሊክ እንዳሁን ፈትሻት
> ባያይህ ነውና ጠላትህ የሚሻት!

በሌላ በኩል ደግሞ በተለያየ መንገድ ያታልሏቸው ነበር። በወቅቱ ኢትዮጵያውን በባዶ እግራቸው የሚሄዱም ስለነበሩ የእግራችንን ዳና እየተከተለ ጠላት ያጠቃናል ብለው የጠረጠሩ አርበኞች አንድ ዘዴ ፈጠሩ። ለምሳሌ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ መሄድ ፈልገው ከሆነ የእግር ዳና በመፍጠር ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ይሄዳሉ። ከዚያም የእግር ዳና ሳይፈጥሩ ወደ ምዕራብ ይመለሳሉ። ጠላት ወደዚያ የሄዱ መስሎት ዳና ተከትሎ ሲሄድ ከኋላ ያጠቁት ነበር።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የጀግንነትን ነገር እናንሳ ከተባለ እያንዳንዱ ዕለት ጀብዱ የተፈጸመባት ትሆናለች። ዳሩ ግን ሦስት ቀኖች ደግሞ በተለየ መልኩ ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸው ናቸው። የካቲት 12፣ የካቲት 23 እና ሚያዚያ 27 በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ልዩ ቦታ አላቸው። የካቲት 12 ግፈኛው ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያውያንን የጨፈጨፈበት ሲሆን ፣ የካቲት 23 የአድዋ ድል ፣ሚያዚያ 27 ጀግኖች አርበኞች አምስት አመት ሙሉ ፋሽስት ጣልያንን ተዋግተው ያሸነፉበት የድል በአል ናቸው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸው እነዚህ ሦስት ቀናት ከጣሊያን ወረራ ጋር የተያያዙ ናቸው።

እነዚህን ሁሉ ድሎች ከየት አመጣናቸው ከተባለ፤ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ የኢትዮጵያ ባህልና ጥበብ ስለሆነ ነው። ለዚህም ነው የጥበብ ሥራዎቻችን ጀግንነትን ገላጭ የሆኑት። እነዚህ የጥበብ ሥራዎች ደግሞ የህዝብ የቃል ግጥሞች ናቸው። የመድረክ ቴአትሮች ወይም ፊልሞች ቢሆኑ ኖሮ ከእነዚህ ድሎች በኋላ የታሰበ ሊመስለን ይችል ነበር። እንዲያውም ፊልሞቻችን ናቸው ሕዝባዊ የጥበብ ሀብቶቻችንን መነሻ አድርገው የተሰሩት።

ዛሬ የአርበኞችን ቀን እያከበርን ነው። ቀኑ የተለያዩ ታሪካዊ ክስተቶችን በማስታወስ ይከበራል። በዚህ ዓምድ ደግሞ አርበኝነትን የሚገልጹ የሕዝብ ቃል ግጥሞችን እናስታውሳለን።

የኢትዮጵያ ጀግኖች ስማቸው ሲነሳ
በሩቅ ያስፈራሉ እንደ ዱር አንበሳ

ይህ የአርበኝነት ስንኝ በተለይም በዘፈኖች ውስጥ ነው የሚሰማው። ምናልባትም መነሻው የሕዝብ ሆኖ ይሆናል በብዙ የአርበኝነት ዘፈኖች ውስጥ የምንሰማው፤ እንዲህ እንደ አርበኞች ቀን አይነት የድል በዓል ሲከበር ደግሞ ኢትዮጵያውያን በቡድን በቡድን ሆነው በሕብረ ዝማሬ ይጫወቱታል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ጀግንነት ባህል ነው ብለናል። ኢትዮጵያዊ መደፈርን አይቀበልም፤ ይህ መደፈርን ያለመቀበል ባህል ነው ወራሪን ሁሉ እያሳፈረ የመለሰው። ለዚህ የጀግንነት ባህል ደግሞ ፉከራዎቻችን ምስክር ናቸው። ትዕግስትንም ይችልበታል፤ ታግሶ ታግሶ ካልሆነ ግን ልኩን ያሳየዋል።

እልም ነው ውሃ አይላመጥም
ጠላት ወዳጅ ላይሆን አልለማመጥም!

ይህ ስንኝ የሚነግረን ጠንካራ አለመሆንን ሳይሆን ጠላትን በቆራጥነት የመዋጋትን ፋይዳ ነው። የፈሩኝ ከመሰለው ጭራሽ እየባሰበት ነው የሚሄድ። በነገራችን ላይ በኢትዮጵያ የጀግንነት ባህል ውስጥ ፀብን ቀድሞ መጀመር የፈሪ ምልክት ነው። ኢትዮጵያውያን ጸብ የማይቀር ከሆነ ይዋጣልን ብለው ይፋጠጣሉ፤ መሳሪያ እስከማስመረጥ ይደርሳሉ እንጂ ቀደመው አይጀምሩም፤ በሌላም በኩል ጀግና ማለት በትዕግስት የሚያሸንፍ መሆኑን ይገነዘባሉ። ታግሰው ታግሰው አውጥተው አውርደው የማያዳግም እርምጃ ይወስዳሉ፤ አትድረሱብን ባይ ናቸው ፤ ሲደረስባቸው ደግሞ አይምሩም።

ኢትዮጵያውያን ጀግንነትን ከነብር ጋርም ያመሳስሉታል።

ቆራጥ ጎበዝ እና ነብር አንድ ናቸው
ሰው ደርሰው አይነኩም ካልደረሱባቸው! ይላሉ።

ነብር በባህሪው እንደ ሌሎች እንስሳት ቀድሞ የመተናኮል ባህሪ የለውም፤ ከተተናኮሉት ግን አይለቅም። የጦር መሳሪያ የያዘ ሰው ሳይቀር ይተናነቃል። የጀግንነት መጀመሪያው ፀብን ቀድሞ አለመጀመር መሆኑን ለመግለጽ ነው ነብርን ተምሳሌት ያደረጉት።

ተመክሮ ተመክሮ አልመለስም ያለ ጠበኛ ዋጋውን ማግኘት እንዳለበት ያምናሉ። ዳግም እንዳያስበው አድርገው አይቀጡ ቅጣት መቀጣት እንዳለበትም ነው የሚያምኑት፤ ለዚህም ይመስላል ፦

በክላሽ መንጥሮ በምንሽር ማረስ
አረም አያበቅልም እስከወዲያው ድረስ እያሉ የሚያንጎራጉሩት።

ከዕለት ከዕለት ሥራዎቻቸው ጋር አገናኝተው ይገልጹታል ማለት ነው። ምንጣሮ ለእርሻ የሚሆን ማሳ ማዘጋጀትን ይመለከታል፤ ዛፎችን፣ ቁጥቋጦዎችንና ሌሎች ነገሮችን በማንሳት መሬቱን ለእርሻ ዝግጁ ማድረግ ማለት ነው። በሚገባ ተመንጥሮና ተለሳልሶ የታረሰ መሬት አረሙ አያስቸግርም። ይህን ሁኔታም በክላሽ መንጥረን መንጥረን ከጣልነው ድጋሚ አያንሰራራም ማለታቸው ለእዚህ ነው።

እነዚህ ጀግኖች አስቀድመው «ተው ሰላም ይሻለናል» ብለው የሚለማመጡ ናቸው። ፈሪ ግን ሲታገሱት የፈሩት ይመስለዋል።

ኧረ ተው አንተ ሰው ስሸሽ አታባረኝ
ለአንተም ግፉ በዛ እኔንም መረረኝ! ይለዋል።

ይህን ብሎት ካልተመለሰ አባራሪው የግፉን ዋጋ ይከፍላል ማለት ነው። አንዳንድ ሀብታም ምናልባት የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ ስላለ የሚፈራ ይመስለው ይሆናል። ምዕራባውያን በኢትዮጵያ ላይ እንደሚያደርጉት ማለት ነው። ለዚህ ደግሞ ቆራጡ ድሃ ፦

አትንኳት ጎጆዬን በአንድ እግሯ ቆማለች
ትልቁን አዳራሽ ይዛው ትጓዛለች! ሲል ይገልጻል።

አንተ ሀብታም ነኝ፣ ባለጊዜ ነኝ ብለህ ብትመጻደቅም የሌሎችን ጎጆ ካላከበርክ ያንተም ህንጻ ይፈርሳል፤ ይደረመሳል፤ እንዲያውም ከእኔ በላይ አንተ ትጎዳለህ ማለቱ ነው።

አሁን ደግሞ ከሕዝብ ስነ ቃል እንውጣና ከፋሽስት ጣሊያን ጋር የተያያዙ ግጥሞችን እንጠቃቅስ። እነዚህ ግጥሞችም መነሻቸው የኢትዮጵያ የጀግንነት ባህል ነው። ግጥሞቹን ከተክለጻድቅ መኩሪያ የታሪክ መጽሐፎች ላይ ያገኘናቸው ናቸው።

ጣሊያን ኮሶ ጭኖ ሸዋን ሊያጠጣው
ገና ሲበጠብጥ ዳኘውን ቀናው
ቅዳሜ ተግዞ እሁድ ተበራየ
መስኮብም ገረመው ጣሊያንም ጉድ አየ!
አገርክን ምኒሊክ እንዳሁን ፈትሻት
ባያይህ ነውና ጠላትህ የሚሻት!

እነዚህ በዓድዋ ጊዜ የተገጠሙ ስንኞች በአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ጊዜም ለኢትዮጵያ አርበኞች ትግል ወኔ መቀስቀሻ በመሆን አገልግለዋል። ጣሊያን ለ40 ዓመታት ያህል ተዘጋጅታ ስትመጣ «እስኪ ያንኑ የለመደችውን መድኃኒት (ጎራዴና ጥይት) ስጧት» ተብሏል።

እስኪ ለጣሊያኖች መድኃኒት ስጧቸው
የሚያስቀምጥ ሳይሆን የሚያስመልሳቸው

በማለትም ኢትዮጵያውያን ተቀኝተዋል። ጣሊያኖችም በድጋሚ በመጣ እግራቸው የእጃቸውን አግኝተው ተመልሰዋል።

የሞሶሎኒ አሽከሮች ሁሉም ሎጋ ሎጋ
ሲመጡ በፈረስ ሲመለሱ በአልጋ

ተብሎላቸዋል። የሞሶሎኒ አሽከር የነበሩት እነ ግራዚያኒ በጀግኖች በእነ ሞገስ አስገዶምና አብርሃም ደቦጭ በምብ ተጥሎባቸው ቆሳስለው ነው ወደ ሀገራቸው የተመለሱት።

በዚህ የአርበኞች ቀን የሚታወሱት በአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ጊዜ የተሳተፉት ብቻ አይደሉም። በአጠቃላይ ኢትዮጵያን ያስከበሩ ጀግኖች ናቸው። ስለዚህ እኛም በአርበኞች ስም ሁሉንም እያመሰገንን ከተወደሱባቸው ስንኞች በሚከተሉት እንሰናበታለን።

በሰራው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ
ተፈፀመ ጣሊያን ሐበሻ እንዳይደርስ
ጣሊያን ሰሀጢ ላይ እግሩን ቢዘረጋ
እንደ ገብስ ቆላው አሉላ አባ ነጋ
ዮሐንስ መብቱን ላሉላ ቢሰጠው
እንደ ቀትር እሳት ቱርክን ገላመጠው
ጣልያንም ወደቀ እያንቀጠቀጠው
አጭዶና ከምሮ እንደ ገብስ አሰጣው!
አሉላ አባነጋ የደጋ ላይ ኮሶ
በጥላው ያደክማል እንኳንስ ተኩሶ!
አሉላ አባነጋ ካስመራ ቢነሳ
ቢቸግረው ጣሊያን አለ ፍርሳ ፍርሳ።
ጣሊያን በሀገርህ አልሰማህም ወሬ?
የበዝብዞች አሽከር የነ ሞት አይፈሬ
ዘለው ጉብ ይላሉ እንደ ጎፈር አውሬ!

# ልዩ ልዩ

## ሚያዝያ 27

**ገርማ መንግሥቴ**

ሚያዝያ 27 አደባባይ (ወይንም በተለምዶ የአራት ኪሎ ሐውልት) ኢትዮጵያ ከታቀደ የጣሊያን አገዛዝ በ1933 ዓ.ም ነፃ ስለወጣችበት ቀን ማስታወሻ የቆመ ታላቅ የድል ሐውልት ነው።

ታሪክ እንደሚሳየው አገራችን ሁለት የኀዘንና የደስታ ቀኖችን ትዘክራለች። ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም የፋሽስት ኢጣልያ ጄነራል ባዶሊዮ በጊዜያዊ ድል አድራጊነት አዲስ አበባን በቁጥጥሩ ሥር ያደረገበትና ነፃነታችንን ያጣንበት ዕለት ሲሆን ልክ በአምስት ዓመቱ በ1933 ዓ.ም ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ በአባት እናቶቻችን የአርበኝነት ትግል፣ በእንግሊዝ እና አጋሮቿ ዕርዳታ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ የገቡበት ዕለት ነው። ይህ ስለ ሚያዝያ 27 ሲነገር ሳይጠቀስ የማይታለፍ እውነት ነው።

«ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለሥላሴ [1923-1967] በተገኙበት እኩለ ቀን 6 ሰዓት ላይ በታላቁ የዳግማዊ ምኒልክ ቤተመንግስት አደባባይ በኢጣሊያ (ሚያዝያ 27 1928 ተሰቅሎ የነበረው) ወርዶ አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ አላማችንን በከፍተኛ አጀብ መልሰው ሰቀሉት...፡፡» በሚል ሁል ጊዜ የሚነገረው አይጠገቤ ታሪክም ስለዚሁ ስለ ሚያዝያ 27 ነውና ዕለቱ ከዕለትም ባለፈ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የህልውና ጉዳይ፤ በደምና በአጥንት የተገኘ የድል ቀን ነውና በዓሉን የማክበር፤ ተንበርክከንም አያት ቅድመ አያቶቻችንን በማስታወስ መዘከር ሲያንሰን ሲሆን፤ በአንድነት በመሞት መስዋእትነት የከፈሉት እኛ በነፃነትና በአንድነት እንድንኖር መሆኑንም በማወቅ የእነሱን አሻራ ማስቀጠል ያለብን መሆኑንም በመገንዘብ ሊሆን ይገባል።

ታላቁ የታሪክ ፀሐፊ አምባሳደር ዘውዴ ረታ (የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት፣ 2005 ዓ.ም)፣ እንደሚነግሩን «በሚያዝያ 27/1928 ዓ.ም የፋሺስትን ግፈኛ ማርሻል ባዶሊዮ አረንጓዴ-ቢጫ-ቀዩን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አስወርዶ፣ ቀይ-ነጭና-አረንጓዴውን ባንዲራ የሰቀለበት ቀን ነበር፡፡» ተብሎ ጣሊያኖችንና የ«አፍሪቃን መቀራመት» ባለሚሎችን ያስጨፈረውን ያህል፤ «ልክ በ5 ዓመቱ፣ ሚያዝያ 27/1933 ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ በከፍተኛ አጀብ እኩለ ቀን ስድስት ሰዓት ላይ ከታላቁ የዳግማዊ ምኒልክ ቤተመንግሥት ዓደባባይ ላይ ሰንደቅ ዓላማችንን መልሰው ሰቀሉት» በሚለው አንገት ያስደፋ ዕለት ነው - ሚያዝያ 27። ይህ ብቻም አይደለም፤ «ሚያዝያ 27 ምንድን ነው?» ለሚሉ ዕለቱ ብዙ የሚባልለት አለና ይከታተሉን።

የአሰቃቀል ሥነሥርዓቱንም በተመለከተ ዘውዴ ረታ፤ ከላይ በጠቀስነው መጽሐፋቸው «የክብር ዘብ ተሰልፎ፣ በራስ አበበ አረጋይ የሚመራው አሥር ሺህ አርበኞች ያሉት ጦር ዙሪያውን በአገር ፍቅርና በብሔራዊ ስሜት እንደቆፈጠነ፣ በሱዳን በኩል የመጣውና በሻለቃ ዊንጌት የሚመራው የጌዲዮን ጦርም ተሰልፎ፣ መድፍ ተደጋግሞ እየተተኮሰ ሰንደቃችን በክብር ከፍ አለ፡፡» በማለት የፃፉለት ነው ሚያዝያ 27።

የታሪክ ባለሙያው አቶ ጥላሁን ጣሰው በTrying Times መጽሐፋቸው «ፋሺስት ጣሊያን በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን የወረረችው፣ በቅኝ በያዘቻቸው በሰሜን በኤርትራ በኩልና በደቡብ ምሥራቅ በኢጣሊያን ሶማሊላንድ በኩል በ400 ሺህ ወታደሮች፣ በ300 የጦር አውሮፕላኖች፣ በ30 ሺህ ተሽከርካሪዎችና በ400 ታንኮች አማካይነት ነበር፡፡ ሙሶሎኒ በወቅቱ የደረሰበትን ሽንፈት ለመቋቋምና ለመቀልበስ የወሰደው እርምጃ ሠራዊቱ በመርዝ ጋዝ እንዲጠቀም ማዘዙ ነው፡፡ የታኅሣሥ 18 ቀን 1928 ዓ.ም የሙሶሎኒ ትዕዛዝ በተምቤንና በሐሸንጌ ሐይቅ ለሺዎቹ እልቂት ሰበብ ሆኗል፡፡» ማለታቸው «በተምቤን ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ ባልሆኑ መሣሪያዎች ድል አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ድል በማድረጉ ፋሺስት የኬሚካል ጥቃቱን ፈጸመ፡፡ በዚያን ጊዜ ያለቁት 700 ሺህ የሚደርሱ ናቸው፡፡» ሲሉም ማከላቸው የተነገረላቸውና የጉዳዩን ሳቢያና ውጤት ያመላከቱባት ነው ሚያዝያ 27። ይህንን የሚያክል ጠላት ያንበረከከ የአባቶቻችን አንድነትና ተጋድሎ ዛሬም ሊቀጥል እንጂ ሊዳለከም ከቶም አይገባውም።

እኛ፣ ዕድሜ ለአያት ቅድመ አያቶቻችንና ልክ እንደ ሚያዝያ 27 ሁሉ ሌሎችም አሉን። በ«ትንሣኤና ሕይወት ሚያዝያ ፳፯ት» መጽሐፍ ላይ እንደ ተገለፀው «የታሪክ ሥፍራዎችና ሜዳዎች፣ የነፃነት ቀኖችና ወሮች ከነዘመናቸው የማይረሱ ናቸው ይላል፡፡ ለምሳሌ ዓድዋና የካቲት 23 ቀን በመቼውም ዘመን በማናቸውም ወርና ቀን ቢሆን ሲታወሱ ትዝ የሚለው፣ በ1888 ዓ.ም. ከጣሊያኖች ጋር ተደርጎ በነበረው ጦርነት የተገኘው ድልና በዚህ ምክንያት በዓለም ላይ ጮራውን የፈነጠቀው የኢትዮጵያ የመታወቅ ዝና ነው፡፡ ድሉም ሲታሰብ አብረው ከሚታሰቡት ከንጉሠ ነገሥቱ ከዳግማዊ አፄ ምኒልክ ጀምሮ ከሠራዊት እስከ መኳንንት የነበሩት የጦር ጀግኖች ናቸው፡፡»

ደራሲው በዚህ አያበቁም፤ «ለአፄ ምኒልክና ለአፄ ኃይለሥላሴ ካሏቸው የድል ቀኖች ዋናዎቹ የካቲት 23 ቀን (1888 ዓ.ም.) እና ሚያዝያ 27 ቀን (1933 ዓ.ም) ናቸው፡፡ ከዚህም አስቀድሞ ለነበሩት ለአፄ ዮሐንስ የድል ቀኖችና ሜዳዎች ነበሯቸው፤ እነ ጉንደት፣ ጉራዕ፣ ሰሐጢና ዶግዓሊ የየራሳቸው የድል ቀኖች አሏቸው፡፡ ከስምንት አሥርታት በፊት የተገኘው የሚያዝያ 27ቱ ድል ለመላው ለአፍሪካ ነፃ አወጣጥ መንገድ ጠራጊ መሆኑንም ያመሠጥራሉ፡፡ ለኢትዮጵያ ድጋፍ በሰጠችው የእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ውስጥ ከቅኝ ግዛቶቿ የአፍሪካ አገሮች የተመለሱት አፍሪካውያን ወታደሮች ኅሊና ውስጥ «እኛም ነፃ መውጣት አለብን!» የሚለው መነሳሳት የታየው በሚያዝያው ድልና ስኬት» ነውም ነው የሚሉት።

በታሪክ እንደተመዘገበው «ኢትዮጵያ ከ1928 ዓ.ም. ሚያዝያ 27 ቀን (አዲስ አበባ በፋሺስት ጣሊያን የተያዘችበት) እስከ 1933 ሚያዝያ 27 ቀን (ፋሺስቱ ተደምስሶ አዲስ አበባ በድል የተመለሰችበት) ድረስ የጠላት ኰቴ በመስኮቿ ላይ ቢዘዋወርም ገዢነቱን አላወቀችለትም፡፡ ጫካው ሁሉ የጀርት ወስፌ ስለሆነበትና ሜዳውም ቢሆን አቃቅማ ብቻ ሆኖ ስላስቸገረው ምን ያህል ጭንቀት እንዳደረበት አምስት ዓመት ያልሞላው የሥቃዩ ዘመን ምስክር ነው፡፡»

ዛሬ እየተከበረ ያለውና ለጣልያን በጥቁር ቀንነቱ የሚታወቀው ሚያዝያ 27 ሌሎችም ለየት ያሉ መገለጫዎች ያሉት ሲሆን፤ አንዱም «በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ከ1934 ዓ.ም. እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ የድሉ በዓል ይከበር የነበረው ሚያዝያ 27 ቀን ሲሆን፣ ከደርግ መንግሥት መምጣት በኋላ በዓሉን ወደ «መጋቢት 28» ለውጦት ከወደቀም በኋላ እስከ 1987 ዓ.ም. ሲከበር ኖሯል፡፡ ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ በወጣ በአምስተኛ ዓመቱ በነባር አርበኞቹና በኅብረተሰቡ ጥያቄ፣ በታሪክ ምሁራንም አረጋጋጭነት በዓሉ በ1988 ዓ.ም ወደ መሠረታዊ ቀኑ ሚያዝያ 27 ቀን ተመልሶ በመከበር ላይ ይገኛል፡፡» የሚለው፤ የአንድን አገር መሪዎች የታሪክ አረዳድ፣ ፖለቲካዊ ማንነት፣ የሚከተሉትን ርእዮትና የሚያራምዱትን እርስ በእርሱ የተጋጨ ሀሳብ የሚያሳየው የታሪክ ትዝብት ነው።

ከሰውም ሰው አለ፤ ከእንጨትም እንደዛው። ባይሆን ኖሮ «ከሰው መርጦ ለሹመት፤ ከእንጨት መርጦ ለታቦት።» ወደ ቀን፣ ወር እና አመትም ስንመጣ ያው ነው። ሁሉም ዓይነት ሁነትና ኩነት የየራሱ ቀን፣ ወር እና አመተ ምህረት አለው። ድምፃዊው «ማን እንደ እናት ...» እንዳለው ሁሉ፤ ቀናት፣ ወራት አመታት ይኑር እንጂ «ማን እንደ ሚያዝያ 27 1933 ዓ.ም» በሚለው ተስማምተን፤ አባቶቻችን ጠንካራ አንድነትና ተጋድሎ ከዛ ችግር እንደወጡት ሁሉ እኛም በአንድነትና ዘመኑ በሚጠይቀው ተጋድሎ ከገጠመን ችግር እንወጣ ዘንድ በማሳሰብ ነው። መልካም በአል!!!

# ዓለም አቀፍ

## ሰሜን ኮሪያ በአምስት ወራት ውስጥ ለ14ኛ ጊዜ የባላስቲክ ሚሳኤል አስወነጨፈች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሰሜን ኮሪያ ያስወነጨፈችው ሚሳኤል በ780 ኪሎ ሜትር ከፍታ 470 ኪሎ ሜትር መብረሩ ተነግሯል። ባላስቲክ ሚሳኤሉ በሰዓት 13 ሺህ 119 ኪሎ ሜትር የሚጓዝ መሆኑ ነው የተገለጸው።



የሰሜን ኮሪያ ባላስቲክ ሚሳኤል

ሰሜን ኮሪያ ወደ ምሥራቃዊ የባህር ዳርቻዋ ባላስቲክ ሚሳኤል ማስወንጨፏን የገለጸው የደቡብ ኮሪያ ጦር ነው። የሴዑል ወታደራዊ አመራሮች እንዳሳወቁት፣ ሰሜን ኮሪያ የባላስቲክ ሚሳኤሉን በፒዮንግያንግ ሱናን አካባቢ ከጠዋቱ 12፡ 03 አካባቢ ነው ያስወነጨፈችው።

የጃፓን የባህር ዳርቻ ጠባቂዎችም ሰሜን ኮሪያ ከባድ መሣሪያ መተኮሷን አረጋግጠው፤ የተተኮሰው መሣሪያ ባላስቲክ ሚሳኤል ሊሆን ይችላል ብለዋል።

የደቡብ ኮሪያ ወታደራዊ አመራሮች፤ ሰሜን ኮሪያ ያስወነጨፈችው አዲሱ የባላስቲክ ሚሳኤል በ780 ኪሎ ሜትር ከፍታ 470 ኪሎ ሜትር መብረሩን ያስታወቁ ሲሆን፤ ሚሳኤሉ በሰዓት 13 ሺህ 119 ኪሎ ሜትር የሚጓዝ መሆኑን አስታውቀዋል።


ሰሜን ኮሪያ የፈረንጆቹ 2022 ዓመት ከገባ ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ የዛሬውን ጨምሮ 14 የሚሳኤል ሙከራዎችን ማድረጓ ይታወሳል።

ፒዮንግ ያንግ ባሳለፍነው ወር ከፈረንጆቹ 2017 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ አህጉር አቋራጭ ባላስቲክ ሚሳኤል ማስወንጨፏም ይታወሳል።

የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን ከቀናት በፊት በተከበረው የአገሪቱ ጦር ኃይሎች ምስረታ ቀን ላይ ባደረጉት ንግግር ነው፤ «ፒዮንግያንግ አሁንም ቢሆን የኒውክሌር ጦር መሣሪያ እድገትን ለማፋጠን ጠንክራ ትሠራለች» ማለታቸው ይታወሳል።

ሰሜን ኮሪያ ባለፍነው ወር «አውሬው» የሚል መጠሪያ የተሰጠውን ግዙፉን ህዋሰአንግ-17 አህጉር አቋራጭ ሚሳኤል (አይ.ሲ.ቢ.ኤም) ሙከራ ማድረጓ ይታወሳል።

የዘርፉ ባለሙያዎች «ህዋሰአንግ-17» ሚሳኤልን «ግዙፉ» ወይም «አውሬው» ሲሉ የሚጠሩት ሲሆን፤ ሚሳኤሉ አህጉር አቋራጭ (አይ.ሲ.ቢ.ኤም) ሚሳኤል ዓይነት ነው።



የጋዝ ቧንቧ መስመር

## የአውሮፓ ኅብረት የሩሲያ የተፈጥሮ ጋዝን ለመተካት አፍሪካን እያማተረ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ከ10 በላይ የአውሮፓ አገራት ነዳጅ በሩብል ከሩሲያ በመግዛት ላይ ናቸው፡፡

ኅብረቱ እስከ ፈረንጆቹ 2030 ድረስ 50 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ጋዝ ለመግዛት አቅዷል፡፡

የአውሮፓ ኅብረት ከሩሲያ የሚገዛውን የተፈጥሮ ጋዝን ለመተካት ፊቱን ወደ አፍሪካ ማዞሩ ሪፖርት አመልክቷል፡፡

ከአውሮፓ ኅብረት የተገኘ ረቂቅ ሰነድን ዋቢ አድርጎ ብሉምበርግ ባወጣው ሪፖርት፤ በአፍሪካ ውስጥ ያሉ እንደ ናይጄሪያ፣ ሴኔጋል እና አንጎላ ያሉ አገራት በአብዛኛው ጥቅም ላይ ያልዋለ ከፍተኛ ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት አላቸው።

ኅብረቱ በፈረንጆቹ እስከ 2030 ድረስ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባውን ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ በ50 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ለማሳደግ እቅድ እንዳለውም ተመላክቷል።

ለዚህም ኅብረቱ ከሩሲያ በስተቀር ወደ ሌሎች አገራት የጋዝ ቧንቧ መስመር ጨምሮ በተለያዩ የጭነት አማራጮች የሚያስገባውን የጋዝ መጠን ለመጨመር ማቀዱ ተገልጿል።

እንደ ሪፖርቱ ከሆነ የአውሮፓ ኅብረት እቅዱን ለማሳካት ከአሜሪካ ጋር ያለውን የፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ አቅርቦት ስምምነትን ሙሉ በሙሉ መተግበር አለበት፡፡

እንዲሁም እንደ ግብፅ፣ እስራኤል፣ አዘርባጃን እና አውስትራሊያ ካሉ አቅራቢዎች ጋር ያለውን የንግድ ስምምነት ማጠናከር እንደሚጠበቅበትም ተመላክቷል።

ሩሲያ ከመጋቢት መጨረሻ ቀናት ጀምሮ አውሮፓ ኅብረትን ጨምሮ ወዳጅ ላልሆኑ ለሌሎች አገራት ነዳጅ በሩብል እንዲሸጥ መወሰኗ ይታወሳል።

የአውሮፓ ኅብረት የሩሲያን አዲስ የነዳጅ ግዥ ውሳኔ ውድቅ ያደረገ ቢሆንም የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን በበኩሉ ማዕቀቡን ሳይጥሱ የአውሮፓ የነዳጅ ኩባንያዎች ከሩሲያ በሩብል እንዲገዙ ፈቅዷል።

ከ10 በላይ የአውሮፓ አገራት ነዳጅ በሩብል ከሩሲያ በመግዛት ላይ ሲሆኑ ፖላንድ እና ቡልጋሪያ ነዳጅ ለመግዛት ሩብል ባለማቅረባቸው ምክንያት ሩሲያ ነዳጅ መሸጥ ማቆሟ አይዘነጋም።

ቻይና ባሳለፍነው ተመሳሳይ ወራት ከሩሲያ የገዛችው የነዳጅ መጠን ከዘንድሮው ጋር ሲነጻጸር በ60 በመቶ ማደጉን የወጣ ሪፖርት ያመለክታል።

# ስፖርት





# የዓለም ዋንጫ በኢትዮጵያ

**ብርሃን ፈይሳ**




ፎቶ ናኦል አየለ

**መግለጫው በተሰጠበት ወቅት**

በእግር ኳስ የየትኛውም ኮከብ ሕልምና የመጨረሻ ስኬት የዓለም ዋንጫን ከመሳም የበለጠ ሊሆን አይችልም። ይህ ታላቅ ዋንጫ ትልቅ ከበሬታ ከሚሰጣቸው የስፖርት ሽልማቶች መካከል አንዱ ስለመሆኑም በርካቶች ይስማማሉ። ይህን ታላቅ ዋንጫ ለማየት ወይም ለመሳም የሚታደሉት ግን እጅግ ጥቂቶች ናቸው። በመሆኑም ይህን ዋንጫ የማየትም ይሁን የመንካት እድል የሌላቸው የዓለማችን እግር ኳስ አፍቃሪዎችን ታሳቢ በማድረግ የዓለም ዋንጫ ውድድር በየአራት ዓመቱ በተለያዩ የዓለም ሃገራት ከመካሄዱ አስቀድሞ ዋንጫው በተለያዩ ሃገራት በመዘዋወር የስፖርት ቤተሰቡ ፎቶ አብሮት እንዲነሳ ይደረጋል። በዚህ ዓመትም የዓለም ዋንጫ በኳታር የሚካሄድ መሆኑን ተከትሎ ዋንጫው በተመረጡ አገራት እየተዟዟረ በስፖርት ቤተሰቦች እየተጎበኘ ይገኛል። ይህን ታላቅ ዋንጫ ለማንሳት ባልታደለችው አፍሪካም በመጪው ግንቦት ወር አጋማሽ ይመጣል። ኢትዮጵያም ዋንጫው መዳረሻውን ከሚያደርግባቸው የአፍሪካ አገራት አንዷ እንደምትሆን ታውቋል።

የዓለም ዋንጫው በአፍሪካ ዘጠኝ ሃገራት ሲዘዋወር መዳረሻውን በኳታሩ ዓለም ዋንጫ ተሳታፊ በሆኑ አምስት ሃገራት ያደርጋል። ሴኔጋል፣ ሞሮኮ፣ ጋና፣ ካሜሮን እና ቱኒዚያ የዓለም ዋንጫው ተሳታፊ እንደመሆናቸው እድሉን ከሚያገኙት መካከል ናቸው። ኢትዮጵያን ጨምሮ አራቱ ሃገራት ደግሞ በውድድሩ ተካፋይ የማይሆኑ የተመረጡ የዋንጫው መዳረሻ ሃገራት ናቸው። የዓለም ዋንጫው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ይህ ለሶስተኛ ጊዜ ሲሆን፤ በመጪው ግንቦት 16 እና 17/2014 ዓ.ም የሁለት ቀናት ቆይታ ይኖረዋል። በዚህ መርሐ ግብር ላይም የእግር ኳስ ቤተሰቡ ከዋንጫው ጋር ፎቶ የመነሳት ዕድል የሚያገኝ ይሆናል፡፡

ከዋንጫው ጋርም ውድድሩን በማሸነፍ ስኬታማ መሆን የቻለ አንድ የእግር ኳስ ተጫዋች ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር ትናንት በሰጡት መግለጫ ጠቁመዋል። እኤአ በ1998 የዓለም ዋንጫ አሸናፊ የሆነው የፈረንሳይ ብሔራዊ ቡድን አባል የነበረው ተጫዋች ዴቪድ ትሬዜጌት ከዋንጫው ጋር በኢትዮጵያ የሁለት ቀናት ቆይታ እንደሚኖረው ታውቋል። ተጫዋቹ ሃገሩ ለዋንጫ በደረሰችበት ጨዋታ ወርቃማ ግብ በማስቆጠር የሚታወቅ ሲሆን፤ በፊፋ 100 በሕይወት ያሉ ምርጥ ተጫዋቾች መካከል አንዱ እንደሆነ ይታወቃል።

የዓለምን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራው ፊፋ ውድድሩን ሲያዘጋጅ ለረጅም ዓመታት በስፖንሰርነት አጋር የሆነው ኮካ ኮላ የመጠጥ ፋብሪካ ይህንን መርሐ ግብር አዘጋጅቶታል። በትናንቱ መግለጫ ላይ የኮካ ኮላ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ዳረን ዊልሰን፤ ታሪካዊ የሆነው የዓለም ዋንጫ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱን አብስረዋል። ድርጅቱ እኤአ ከ1976 ጀምሮ ከፊፋ ጋር በአጋርነት እየሠራ ያለ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ደግሞ ከ60 ዓመታት በላይ ቆይታ እንዳለው ተጠቅሷል። ዘንድሮም ዓለም ዋንጫ የሚካሄድበት ዓመት መሆኑን ተከትሎ «ማመን የተዓምር መሠረት ነው» በሚል መሪ ሃሳብ ደጋፊዎች ከዋንጫው ጋር ፎቶ የመነሳት ዕድል እንዲያገኙ ትክክለኛው ዋንጫ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ መደረጉ ተገልጿል።

በመግለጫው ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ጅራ በበኩላቸው፤ «ኢትዮጵያ ይህንን ዕድል ካገኙት ሃገራት መካከል አንዷ መሆኗ ትልቅ ትርጉም እንዳለው አንስተዋል። ሕልመኛ መሆንና ለስኬትም ጠንክሮ መሥራት አስፈላጊ ነው። ኳታር ትንሽ ሕዝብ ያላት ትንሽ ሃገር ብትሆንም ሕልሟ ትልቅ በመሆኑ ይህንን ውድድር ለማዘጋጀት ችላለች። ከተመልካችነት ወደ ተሳታፊነት መግባት የሚቻለውም ጠንክሮ በመሥራት ነው፡፡» በማለት ከዋንጫው ጀርባ በማዘውተሪያ እና በተጫዋቾች ልማት ላይ መሥራት ከተቻለ የማይደረስበት ነገር እንደሌለ ማየት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ዋንጫው በሕይወት ዘመን አንዴ እና ሁለቴ አልያም ከነጭራሹ የማይገኝ እድል በመሆኑ የሃገራችንን ክብር በሚመጥን ደረጃ ለሁለት ቀናት እንደሚስተናገድ የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ የኮካ ኮላ ድርጅት ዋንጫው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ በማድረጉ በራሳቸውና በኢትዮጵያ ህዝብ ስም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በበኩላቸው፤ ሚኒስትሩም ሆነ መንግሥት ከዓለም ዋንጫ መምጣት ጋር በተያያዘ ከኮካ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል። ሃገሪቷ በውድድሩ የመሳተፍ እድል ባታገኝም የዋንጫው መምጣት ግን አሁን ካለችበት ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር ሰላማዊነቷን የሚያበስር እንደሚሆን ተናግረዋል። ስፖርት ለሃገራት ገጽታ ግንባታ ካለው ፋይዳ ባለፈ ትውልዱ ዋንጫውን በቅርበት በመመልከት ለነገ እንዲያልምና ተግቶ እንዲሠራ የሚያደርገው መሆኑንም አስረድተዋል።

ከዋንጫው ጋር ፎቶ የመነሳት እድል የሚያገኙ የስፖርት ወዳጆችም አስቀድሞ የኮካ ኮላ ጠርሙሶች ላይ የሚገኘውን ምልክት 10 እስኪሞላ አጠራቅመው ወደ ኩዊንስ ሱፐርማርኬት በመሄድ የመግቢያ ካርድ ማግኘት የሚችሉ መሆኑ ተጠቁሟል።

## ማስታወቂያ

በከሳሽ ኢንቨስት ስትሮይ ፕሮጀክት የኢትዮጵያ ቅርንጫፍና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር አዋሽ ወልዳይ ጠቅላላ ሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ለግንቦት 08 ቀን 2014 ከሰዓት በኋላ በ10 ሰዓት ልደታ ከፖሊስ ሆ/ል ጀርባ በሚገኘው ናዛሪን ቤ/ክርስቲያን ሕንጻ 3ኛ ፎቅ ላይ ይቅረብ፡፡

## አማራ ክልል

ንብረትነቱ አህመድ ሲያር ኮድ -3-14500 አ.ማ ተሽከርካሪ የኋላ/የፊት/ ሰሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ ምትክ ሰሌዳ እንዲቀረጽላቸው በ6/8/2014 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ጠይቀውናል። ስለሆነም ይህን ሰሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገባኛል የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ማሳገጃውን ካላቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአ/ብ/ክ/መ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ የሰ/ሸዋ ዞን መ/ትራ መምሪያ የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

ከሳሽ አቶ መኳንት አየነው
ተከሳሽ ደባሽ በርሄ
ተከሳሽ በተከሰሱበት ገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ በቀጠሮው ለ11/09/2014 ዓ.ም. በ3፡00 ሰዓት ምዕ/ጎን/ዞን/ከፍ/ፍ/ቤት ፍታብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ጉዳዩ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምዕራብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ቡድን**

## በደቡብ ክልል

በከሳሽ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ እና በተከሳሾች 1ኛ ዶ/ር አዛገፉ ዳትኮ 2ኛ ዶ/ር ጉንጫሳ አንኮሳ መካከል ባለው የገንዘብ ክስ መነሻ ተከሳሾች ባሉበት አስፈላጊውን ለመስራት ለ10/09/2014 ዓ.ም. ለሆነው ቀነ ቀጠሮ ወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍትሐብሔር ችሎት እንዲያቀርቡ ሆኖ ባይቀርቡ ግን ክሱ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን እንዲያውቁት ሲል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ መንግሥት የወላይታ ዞን ከ/ፍ/ቤት መደበኛ የፍትሐብሔር ችሎት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች፡- አቶ ታምራት ከበደ በቤተማሪያም እና በተጠሪ፡- ወ/ሮ ብርቱካን ተስፋዬ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ተኛ ቤተሰብ እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሑፍ እና ክስ ለመስማት ለ19/9/2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ትግዕስትና ቤዛ ት/ቤት ሀ*/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A60630 የተሽከርካሪው አይነት አውቶቡስ (ከ11 የበለጠ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር LKLSICSBX7A125121 ሞዴል KLQ6728GMIDI የሞተር ቁጥር 69462618 የሊብሬ ቁጥር 001307/262768 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ12/7/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገባኛል የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የን/ስ/ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሞገስ ደነቀ ተፈራ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B41575 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር MBHZ F6C13 NG16 8009 ሞዴል ZF6C1 የሞተር ቁጥር K12MP4284432 የሊብሬ ቁጥር 341650 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ19/8/2014ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ንጋት ሽምዬ ብርሃኔ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A07706 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5BLSF0LN678306 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD615.47*200907030287* የሊብሬ ቁጥር 0238683 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ18/8/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ሰሌዳው ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ትእግስት እና ቤዛእስኩ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A09548 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JT132LNB809027179 ሞዴል LN110L-CRMDSW የሞተር ቁጥር 2L-4156442 የሊብሬ ቁጥር 299838 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ12/7/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገባኛል የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ትዕግስት ባዩ አልታዬ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A47154 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር KZJ950033720 ሞዴል PRADO የሞተር ቁጥር 1KZ-0412441 የሊብሬ ቁጥር 524287 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ22/7/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገባኛል የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

አመልካች፡- አቶ ሚካኤል አክሊሉ እና በተጠሪ፡- ወ/ሮ ትዕግስት አለነ ገ/መድህን መካከል ስላለው የቤተሰብ ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ተኛ ቤተሰብ እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሑፍ በሬጅስትራር በኩል ክስ ለመስማት ለ18/9/2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም መሀመድ ሳኒ ሱቢ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-34863 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሺ ቁጥር JAAKP34G467P11463 ሞዴል NPR-66 የሞተር ቁጥር 4HF1-390874 የሊብሬ ቁጥር 198925/ 238435 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ19/8/2014 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**